# ወንጌላት

ትምህርት
አራት

## የሉቃስ ወንጌል

ተርጓሚ፡ እሸቴ በለጠ

THIRD MILLENNIUM
MINISTRIES

Biblical Education. For the World. For Free.

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ  አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጉሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. In 2009 ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሌ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ጎብኙ፡፡

## ማውጫ


1. **መግቢያ**
2. **ዳራ**

ሀ. ጸሐፊ

1. ትውፊታዊው አመለካከት
2. ግለ ታሪክ

ለ. ቀደምት ተደራሲያን

1. ቴዎፍሎስ
2. ሰፊው ተደራሲያን

ሐ. ወቅት

1. ቀን
2. ዓላማ

3. **መዋቅርና ይዘት**

ሀ. የኢየሱስ ጅማሬዎች

1. የልደቱ መታወጅ
2. ልደትና የልጅነት ወራት
3. ዮሐንስ ኢየሱስን ያመሳሰለበት መንገድ
4. የእግዚአብሔር ልጅነቱ መረጋገጡ

ለ. በገሊላ የኢየሱስ አገልግሎት

1. ስብከት በናዝሬት
2. ማስተማርና ተዓምራት
3. መጥምቁ ዮሐንስ
4. ማስተማርና ተዓምራት
5. የዐሥራ-ሁለቱ ሐዋርያት ዝግጅት

ሐ. የኢየሱስ ወደ ኢሩሳሌም ጉዞ

1. የደቀመዝሙርነት ባህርይ
2. የግጭት መባባስ
3. ደቀመዝሙርነት የሚስከፍለው ዋጋ
4. የኢየሱስ መሰጠት

መ. በኢየሩሳሌምና በአካባቢዋ የኢየሱስ አገልግሎት

ሠ. የኢየሱስ ስቅለትና ትንሣኤ

1. መያዝ፣ ለፍርድ መቅረብና ሞት
2. ትንሣኤ እና ዕርገት

4. **ዐቢይ መሪ ሃሳቦች**

ሀ. የድነት መግለጫ

ለ. እግዚአብሔር  አዳኝ

1. የእግዚአብሔር ኃይል
2. የእግዚአብሔር ዕቅድ
3. የእግዚአብሔር ልጅ

ሐ. የዳኑ ሰዎች

5. **ማጠቃለያ**

# መግቢያ

ከጥቂት ዓመታት በፊት፣ ሰዎች በቃጠሎ ላይ ባለ ህንፃ ውስጥ ሰዎች መውጫ አጥተው እንደነበር የተዘገበ ዜና ነበር፡፡ አንድ ወጣት ግን ወደ ክፈል ጥሶ ገባና ከዚያም ወደ ደህና ስፍራ የሚወስደውን ድምፁን ተከተሉት፡፡ በሕይወት ከተረፉት ሰዎች የተደመጠው ታሪክ እንደሚያስረዳው ያ ሰው በህንፃው ላይ አገልግሎት ለመስጠት በበጎ ፈቃዱ የተሰለፈ የእሳት አደጋ ተከላካይ ነበር፡፡ በእሳቱ ውስጥ የራሱን ሕይወት ቢያጣም፣ ግን ካለቀለት የሞት አደጋ ብዙዎችን አድኗል፡፡

ከሌሎቹ የወንጌላት ፀሐፊዎች በበለጠ፣ ሉቃስ ኢየሱስን አዳኝ አድርጎ ገልፆታል፡፡ አወቅነውም አላወቅነውም፣ የሰው ዘር የጠፋና አሳዛኝ፣ የሚረዳው የሌለና ተስፋ የሌለው ነው፡፡ ከሚጠብቀን ከእግዚአብሔር ፍርድ ልናመልጥ የምንችልበት መንገድ አልነበረንም፡፡ የሉቃስ ወንጌል ግን የራሱን ሕይወት ዋጋ አድርጎ በማቅረብ፣ ሊያድነን ኢየሱስ መጣ፡፡

ወንጌላት በተሰኘው ተከታታይ ትምህርታችን ይህ አራተኛው ሲሆን፣ "**የሉቃስ ወንጌል**" የሚል ርዕስ ሰጥተነዋል፡፡ በዚህ ትምህርት፣ የአዲስ ኪዳኑን ሦስተኛ ወንጌል በላቀ መረዳት የምንመረምረው ሲሆን፣ ትምህርቶቹንም በሕይወታችን እንዴት እንደምናዛምድ እንመለከታለን፡፡

የሉቃስን ወንጌል በሦስት ደረጃዎች እንመለከተዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ የሉቃስን ወንጌል ዳራ እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ አወቃቀሩንና ይዘቱን እንመረምራለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ ጥቂቶቹን ዐቢይ ርዕሰ ጉዳዮቹን እንመለከታለን፡፡ እስኪ በሉቃስ ወንጌል ዳራ እንጀምር፡፡

# ዳራ

የሉቃስን ወንጌል ዳራ የምንመረምረው ጸሐፊውን፣ ቀደምት ተደራሲያኑን እና የተጻፈበትን ወቅትና ሁኔታ በመመልከት ነው፡፡ አስቀድመን ጸሐፊውን እንመልከት፡፡

## ጸሐፊ

ገና ከወዲሁ፣ የሉቃስ ወንጌል ከባለ ሁለት መድብል ሥራዎቹ የመጀመሪው ተደርጎ በስፋት የሚታወቅ መሆኑን እንገልፃለን፡፡ ሁለተኛው የሐዋርያት ሥራ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት፣ የሉቃስ ወንጌል ጸሐፊን ማንነት አስመልክቶ የሚነሱ ጥያቄዎች የሚደመደሙት በሐዋርያት ሥራ ጸሐፊ ማንነት ላይ በሚነሱ ጥያቄዎች ይሆናል፡፡ እስኪ በሉቃስ ፩፥1-4 የተጠቀሰውን የሉቃስን ወንጌል መቅድም አድምጡ፡፡

> ***የከበርህ ቴዎፍሎስ ሆይ፥ ከመጀመሪያው በዓይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት እንዳስተላለፉልን፥ በኛ ዘንድ ስለ ተፈጸመው ነገር ብዙዎች ታሪክን በየተራው ለማዘጋጀት ስለ ሞከሩ፥ እኔ ደግሞ ስለ ተማርኸው ቃል እርግጡን እንድታውቅ በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትዬ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ። (ሉቃስ 1፥4)***

እስኪ በሐዋርያት ሥራ 1፥1-2 ከተመዘገበው ተመሳሳይ መቅድም ጋር አነጻጽሩት፡

> ***ቴዎፍሎስ ሆይ፥ ኢየሱስ የመረጣቸውን ሐዋርያትን በመንፈስ ቅዱስ ካዘዛቸው በኋላ እስከ ዐረገበት ቀን ድረስ፥ ያደርገውና ያስተምረው ዘንድ ስለ ጀመረው ሁሉ መጀመሪያውን ነገር ጻፍሁ፤ (የሐሥ 1፥1-2)***

ሁለቱም መቅድሞች እንደሚያመለክቱት ጸሐፊው የጻፈው ቴዎፍሎስ ለተባለ ሰው ነበር፡፡ የሐዋርያት ሥራው መቅድም የቀደመውን መጽሐፍ ያጣቅሳል፡፡ ይህም አብዛኞቹን ምሁራን የቀደመው መጽሐፍ የሉቃስ ወንጌል ነው ወደሚል ድምዳሜ መርቷቸዋል፡፡

ሁለቱንም መጻሕፍት ተመሳሳይ ሰው እንደጻፋቸው የሚስረዳ ሌላም ማስረጃ አለ፡፡ በሉቃስ ወንጌል ውስጥ የሚገኘው የግሪኩ አጣጣል፣ ከሐዋርያት ሥራው የግሪክኛ አጣጣል ጋር ተመሳሳይ ሲሆን፣ ከሌሎቹ ወንጌላት አጣጣል ግን በጣም ይለያል፡፡ መጻሕፍቱ በተጨማሪም በተመሳሳይ መሪ ሃሳቦች ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ፡፡ የወንጌልን ዐለም አቀፋዊነት፣ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ፣ ማንም ሊቋቋመው ስለማይችለው የእግዚአብሔር ፍቃድና ቃል እና የክርስቶስን ሥራ ከ"ድነት" ጋር አጣምሮ መግለጥ፡፡ እንግዲያው፣ ሁለቱንም አንድ ጸሐፊ ጻፋቸው ካልን፣ ያ ሰው ማን ነበር?

የሦስተኛውን ወንጌል ጸሐፊ በሁለት እርከኖች እንመረምራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ወንጌሉ ሉቃስ በሚባል ሰው ተጽፏል የሚለውን ትውፊታዊ አመለካከት እናያለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ የሉቃስን ግለ ታሪክ እንመረምራለን፡፡ አስቀድመን ወንጌሉን ሉቃስ ጽፎታል የሚለውን ትውፊታዊ አመለካከት እንመልከት፡፡

## ትውፊታዊ አመለካከት

በቴክኒክ ረገድ የሉቃስ ወንጌል የጸሐፊውን ስም ስለማይጠቅስ የጸሐፊው ስም አይታወቅም፡፡ ይህ ግን አያስገርምም፡፡ ቴዎፍሎስ ማን እንደጻፈው በእርግጥ ያውቃል፣ ስለዚህ ጸሐፊው ስሙን መጥቀስ አላስፈለገውም፡፡ ሆኖም፣ ስለ ጸሐፊው ማንነት የሚናገሩ ብዙ የመረጃ ምንጮች አሉን፡፡

ወንጌሉን ሉቃስ ጽፎታል የሚለውን ትውፊታዊ አመለካከት የሚያጸኑ ቢያንስ ሦስት ዓይነት ማስረጃዎች አሉ፡፡ በመጀመሪያ፣ በሌሎቹ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች የሚገኙ ጥቆማዎች የእርሱን ጸሐፊነት ይጠቁማሉ፡፡

አዲስ ኪዳን የሦስተኛው ወንጌል ጸሐፊ በሐዋርያው ጳውሎስ የኋለኛ አገልግሎት አብሮት እንደ ነበር ያመለክታል፡፡ ለምሳሌ፣ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ፣ ጸሐፊው አንዳንድ ጊዜ በሦስተኛ መደብ "**እነርሱ**" እያለ ሲጠቅስ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በአንደኛ መደብ "**እኛ**" በማለት ይጠቅሳል፡፡ የእነዚህ የአንደኛ መደብ ትረካዎች መጨረሻ በሐሥ 27፥1-28፥16 የሚገኘውና ጳውሎስ ወደ ሮም ያደረገውን ጉዞ የሚገልጸ ው ነው፡፡

ከዚህ ባሻገር፣ የጳውሎስ ደብዳቤዎች በዚያን ወቅት አብረውት ከነበሩት ጥቂት ሠራተኞች መካከል ሉቃስ አንዱ እንደነበር ይጠቅሳሉ፡፡ ለምሳሌ፣ በ2ኛ ጢሞ 4፥11፣ የጳውሎስ መሞቻ ሲቃረብ፣

“**ሉቃስ ብቻ ከእኔ ጋር አለ**” በማለት ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ነግሮታል፡፡ ይህንን የመሰለው መረጃ ሦስተኛውን ወንጌል የጻፈው ሉቃስ ነው የሚለውን አያረጋግጥም፣ ሆኖም ጠንካራ አዎንታ ይኖረዋል፡፡

ሁለተኛ፣ የሉቃስ ወንጌል ጥንታዊ ቅጂዎች ጸሐፊነቱን ወደ ሉቃስ ይጠቁማሉ፡፡

> **የቀደምት ቅጂዎችን ቀን መለየት በእውነቱ ከፍተኛ ቴክኒካዊ ሳይንስ ነው እናም ምሁራን ለጥንታዊ ቅጂዎች ቀን ለመቁረጥ የሚጠቀሙባቸው ሦስት ጥቃቅን መረጃዎች አሉ፡፡ የመጀመሪያው፣ በእርግጥም እጅግ አስፈላጊ የሆነው፣ (ይህ አንዳንድ ጊዜ ተማሪዎችን ያስገርማቸዋል)ሆኖም እጅግ ወሳኝ የሆነው ፓሊዮግራፊ ነው፡፡ ፓሊዮግራፊ የሚያመለክትው ጥንታዊ ጽሑፍን ሲሆን፣ “ፓሊዮ” ጥንት ማለት ሲሆን “ግራፊ” ደግሞ ጽሑፍ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ጥንታዊ ጽሑፍ ማለት ነው፡፡ ምሁራኑ፣ ማለትም የፓሊዮ ግራፊ ጠበብት በጥቂት የዐሥርት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ስላሉት ይናገራሉ፣ በእርግጠኝነት በሃምሳ ዓመታት ውስጥ ስላሉት ያናገራሉ፣ ምክንያቱም በአንዳንድ ቋንቋዎች የእጅ ጽሑፎች ከጊዜ ወደ ጊዜ የመለዋወጥ አዝማሚያ አላቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ፊደላቱ ራሳቸው ከአጻጻፍ አንጻር ሊለወጡ ይችላሉ፣ የአጻጻፍ መንገዱ ግን መለወጡ አይቀሬ ነው፤ ፓሊዮግራፊ የሚባለውም ያ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የአንድ ነገር ኬሚካላዊ ምርመራ ነው፡፡ የካርቦን ፎርቲን የዕድሜ መለያ ወይም ሌላ ዓይነት መመርመሪያ አለ፣ ያም ቀለሙንም ሆነ የእንስሳት ቆዳውን ዕድሜ ምን ያህል መሆኑን ለማረጋገጥና በዚያም አማካይነት የጽሁፉ ዕድሜ ምን ያህል እንደሆነ ለመለየት የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው፡፡ ሦስተኛው ዘዴ ደግሞ ስለ ጽሑፉ የተነገረ ወይም የተጻፈ ውጫዊ ማስረጃ ነው፡፡ ቅጂዎቹን የሠሩት ፀሐፍት አንዳንድ ጊዜ ቀኑን ይጽፋሉ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የሆነ ማስታወሻ ያስቀምጡብታል ያ እንግዲህ ያ ቅጂ መቼ እንደተከናወነ ለመለየት ይረዳናል ማለት ነው፡፡ እናም የጥንታዊ ቅጂዎችን ዕድሜ የምናጣራባቸው ሦስት የተለያዩ መንገዶች አሉ፡፡ (ዶ/ር ማርክ ስትራውስ)**

ስለ ሉቃስ ወንጌል እጅግ ተዓማኒነት ያለው ጥንታዊ ጽሁፍ በተደጋጋሚ “P-75” የምንለው 75ኛው ፓፒረስ ነው፡፡ ይህ ጥንታዊ ቅጂ በ180 ዓ.ም. አካባቢ እንደተጻፈ ይነገራል፡፡ ይህም ቅጂ ከሌሎች ጥንታዊ ቅጂዎች ይልቅ የሦስተኛውን ወንጌል አብዛኛውን ክፍል ይዟል፣ ርዕሱም “ሉቃስ እንደጻፈው” ይላል፡፡

በርካታ ጥንታዊ ጽሑፎችም የወንጌሉን ጸሐፊ ሉቃስ ያደርጉታል፣ አንድም ጣንታዊ ቅጂ ጸሐፊነቱን ለሌላ የሰጠ አልተገኘም፡፡ ሦስተኛ፣ የመጀመሪያዩቱ ቤተክርስቲያን ጽሑፎችም የሉቃስን ጸሐፊነት አረጋግጠዋል፡፡

ከጥንታዊቷ ቤተክርስቲያን የተገኙ ወሳኝ ዶኩሜንቶች የሦስተኛውን ወንጌል ጸሐፊነት ለሉቃስ ሰጥተውታል፡፡ ከ170-180ዓ.ም. አካባቢ እንደተቀረጸ የሚነገርለት የጥንታዊ የግድግዳ ስዕሎች ግማድ (The Muratoriyan Fragment), የቀደመችው ቤተክርስቲያን እውቅና የሰጠችውን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝሮች የያዘው ጥንታዊ እውቅ ዶኩሜንት ሲሆን፣ የሦስተኛው ወንጌል ጸሐፊ ሉቃስ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

ሌላው ጥንታዊ ምስክር ከ160 እስከ 180 ዓ.ም. እንደተጻፈ የሚነገርለትና የማርሲዮንን የስህተት ትምህርት ለመሟገት የተጻፈው የሉቃስ ወንጌል የጸረ-ማርሲዮን መቅድም ነው፡፡ ሦስተኛውን ወንጌል እንዲህ ያስተዋውቀዋል፡-

**በትውልዱ ከሶሪያዋ አንጾኪያ የሆነውና በሙያው ሐኪም የሆነው ሉቃስ፣ የሐዋርያት ደቀመዝሙር ነበር፡፡ በኋለኞቹ ዘመናትም የጳውሎስ ባልደረባ ሆኖ ነበር… ሉቃስ፣ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት፣ በአካይያ አውራጃ ውስጥ ወንጌሉን ጻፈ፡፡**

ከዚህም በተጨማሪ፣ የሁለተኛውና የሦስተኛው ምዕተ-ዓመታት በርካታ መሪዎች ሉቃስን የሦስተኛው ወንጌል ጸሐፊ አድርገው ተቀብለውታል፡፡ ለምሳሌ፣ የሉቃስ ጸሐፊነት ከ130 – 202 ዓ.ም. በኖረው ኢራኒየስ፤ ከ150 – 215 በኖረው፣ የእስክንድርያው ክሌመንት እና ከ155 እስከ 230 ዓ.ም. በኖረው በተርቱሊያን ተረጋግጧል፡፡

**የሦስተኛው ወንጌል ጸሐፊ ሉቃስ መሆኑን የምናረጋግጥበት ሁሉም ዓይነት መተማመኛ እንዳለን አስባለሁ፡፡ ሉቃስ ሐኪም እንደ ነበር፣ እንዲያው በትንሿ እሲያ ጫፍ አካባቢ በመጣበት ወቅት ጳውሎስ እንዳገኘው ከሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እንረዳለን፡፡ ሉቃስን አገኘው፣ ከዚያው ወደ ፊልጵስዩስ ተጓዙ እናም እንደሚመስለኝ ሉቃስ በህክምናው ሥራ ፊልጵስዩስ ውስጥ ቆየ ከዚያም በ57 ዓ.ም. ወደ ኢየሩሳሌም በተደረገው ጉዞ ከጳውሎስ ጋር ከፊልጵስዩስ ተነሣ፡፡ ስለዚህም ከአዲስ ኪዳን ስለ ሉቃስ የምናገኘው ምስል፣ ጳውሎስን ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ አብሮት የተጓዘ፣ እናም ይኸው ሉቃስ የሉቃስን ወንጌል የጻፈው ያው ሰው መሆኑን የምናረጋግጥበት ሁሉም ዓይነት ማስረጃ አለን ማለት ነው፡፡ (ዶ/ር ፒተር ዎከር)**

**የጳውሎስን ባልደረቦች ተነስታችሁ ልገምት ብትሉ፣ ሉቃስን ላታካትቱ ትችላላችሁ፡፡ ምክንያቱም በጳውሎስ ደብዳቤዎች ውስጥ ወሳኝ ስፍራ ይዞ የምታገኙት ሰው አይደለም፡፡ በቀላሉ የሚቀናችሁ ቲቶን ወይም ሌላውን መገመት ነው፡፡ ስለዚህም በጳውሎስ ደብዳቤዎች ውስጥ ትልቅ ስፍራ ያልተሰጠው የመሆኑ ነገር፣ የሉቃስ ወንጌልና የሐዋርያት ሥራ ጸሐፊ የመሆኑን ነገር ትክክለኛ ያደርገዋል፡፡ ግን በተጨማሪም የወንጌላት ጸሐፊ የሆኑ ሰዎች ማንነት ወንጌላት በቀደምት ጊዜያት በየስፍራው ሲዘዋወሩወደ ነበሩበት ዘመንም ይመልሰናል ብዬም አስባለሁ፡፡ ስለዚህም ሉቃስ ጽፎታል የሚለው ሃሳብና የሐዋርያት ጸሐፊ የሆነው ያው ሰው የጳውሎስም ባልደረባ የመሆኑ ነገር፣ ከጳውሎስ ጉዞዎች በአንዱ አብሮት የተጓዘውና፣ አብሮ ሠራተኛ የነበረው ሉቃስ ሁለቱንም መጻሕፍት ጽፏቸዋል የሚለው በጣም ትክክል ይመስላል፡፡ (ዶ/ር ሪቻርድ ቡከሃም)**

ወንጌሉን ሉቃስ ጽፎታል የሚለውን ትውፊታዊ አመለካከት ካረጋገጥን፣ አሁን ደግሞ የሉቃስ ግለ ታሪክ እንመልከት፡፡

# ግለ ታሪክ

አዲስ ኪዳን ስለ ሉቃስ ግለ ታሪክ ቢያንስ አራት ነገሮችን ይነግረናል፡፡ አንደኛ፣ ሐዋርያ አለመሆኑን፡፡ እንዲያውም፣ በወንጌሉ ለዘገባቸው ለየትኞቹም ነገሮች የዐይን ምስክር የነበረ አይመስልም፡፡ እስኪ በሉቃስ 1፥1-2 የተቀመጡትን ዝርዝሮች አድምጡ፡

> ***የከበርህ ቴዎፍሎስ ሆይ፥ ከመጀመሪያው በዓይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት እንዳስተላለፉልን፥ በኛ ዘንድ ስለ ተፈጸመው ነገር ብዙዎች ታሪክን በየተራው ለማዘጋጀት ስለ ሞከሩ፥ (ሉቃስ 1፥1-2)***

> **የሉቃስ ወንጌል አንድ የታሪክ ጸሐፊ ስለ ታሪኩ ለማስተዋወቅ የሚጽፈውን ዓይነት መግቢያ ከአራቱ ወንጌላት በተለየ መንገድ መቅድም የጻፈ ብቸኛ ወንጌል ነው፡፡ እናም የሚያመለክተው የጊዜውን የታሪክ ዘገባ ከመከተል አንፃር ለየት ያለ ንቃት እንደነበረው ያመለክታል፡፡ እርሱ ራሱን እንደ ዐይን ምስክር ከማቅረብ ይልቅ የዐይን ምስክሮቹን ምስክርነት በመውሰድ ይዘግባል፡፡ ስለዚህ እርሱ የጠቀሳቸው የዐይን ምስክሮች ማረጋገጫ አለን ማለት ነው፡፡ ሆኖም ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ከደረሰ በኋላ፣ ወደ ኢየሩሳሌም ባደረገው የመጨረሻ ጉዞው ሉቃስ ከእርሱ ጋር የነበረበት ጊዜ ነበር፡፡ ጳውሎ ለሁለት ዓመታት በእስር ቤት ነበር፡፡ እናም የሚመስለው ሉቃስ በዚያን ወቅት በኢየሩሳሌም ወይንም በፓለስታይን አካባቢ ቆይቶ እንደ ነበር ነው፡፡ ጥንቁቅ የሆነ የጥንት ታሪክ ጸሐፊ ያደርጋል ተብሎ እንደሚጠበቀውም፣ ሉቃስ ምቹ የሆነ የሁለት ዓመታት ሰዎችን እየተዘዋወረ በቃለ መጠይቅ የማናገር ዕድል አግኝቶ ነበር፡፡ የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን አባላት የነበሩና የጌታ ወንድም የሆነውን ያዕቆብን የመሳሰሉ ሰዎችን ያናግራል፡፡ ያዕቆብ በእርግጠኝነት በዚያ አካባቢ ነበር፡፡ ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያትም አንዳንዶቹ አንድም በኢየሩሳሌም አልያም በፓለስታይን ምድር ዙሪያ ይኖራሉ፡፡ ስለዚህ ሉቃስ ለዐይን ምስክሮቹ ቃለ መጠይቅ ማቅረብ የሚችልበት ምቹ ዕድል ነበረው፡፡ ከዚያም፣ ጳውሎስ ወደ ሮም ሲሄድ አብሮት ስለነበር ስለ ኢየሱስ ታሪክ የሚያስታውሱትን ሁሉ መናገር የሚፈልጉ ሰዎችንም በዚያ የማግኘት ዕድል ነበረው፡፡ ስለዚህ ሉቃስ ከዐይን ምስክሮቹ ጋር በቀጥታ መገናኘት በሚችልበት ምቹ ሁኔታ ላይ ነበር ብዬ አስባለሁ፡፡ (ዶ/ር ሪቻርድ ቡክሃም)**

ሁለተኛ፣ በተጨማሪም ሉቃስ ከአህዛብ ወደ ክርስትና የመጡ አማኞች ያገኘም ይመስላል፡፡ ጳውሎስ ከእስር ቤት ለቆላስይስ ሰዎች ሲጽፍ፣ በዚያን ወቅት አብሮት ከነበረው ከሉቃስ ሰላምታ ይድረሳችሁ ብሎ ጽፏል፡፡ ጳውሎስ በቆላስይስ 4፥14 የጻፈውን አድምጡ፡-

> ***የተወደደው ባለ መድኃኒቱ ሉቃስ ዴማስም ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። (ቆላ 4፥14)***

ይህ ነገር እጅግ ወሳኝነት አለው ምክንያቱም ከቁጥር 10-11፣ ጳውሎስ እንደተናገረው፣ በዚያን ወቅት ከእርሱ ጋር አብረው ሠራተኛ የነበሩትና ከአይሁድ ወገን የሆኑት አርስጥሮኮስ፣ ማርቆስ፣ እና ኢዮስጦስ ብቻ ነበሩ፡፡ ስለዚህ፣ ሉቃስ አህዛብ ነበር ብሎ መደምደም ምክንያታዊ ነው፡፡ ይህም

የሚረጋገጠው በሐሥ 1፥19፣ “ቋንቋቸው” አራማይክ መሆኑን ሉቃስ በመጥቀሱ ነው፡፡ አራማይክ የአይሁድ እንጂ የእርሱ ቋንቋ አልነበረም፡፡

ሦስተኛ፣ ሉቃስ በተጨማሪም በጣም የተማረ ሰው ነበር፡፡ አብዛኞቹ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፉት በተለመደው የግሪክኛ ዘይቤ ነበር፡፡ የሉቃስ ወንጌል ግን በቋንቋ አጠቃቀሙ ረቀቅ ያለ እንደሆነ ይታያል፡፡

ሉቃስ በጣም የተማረ የመሆኑ ነገር በተጨማሪ የተንፀባረቀው በቆላስይስ 4፥14 ጳውሎስ “ሐኪሙ” ብሎ መጥቀሱ ነው፡፡ ምንም እንኳን ህክምና እንደዛሬው መደበኛ የትምህርት ሥርዓት በአዲስ ኪዳን ዘመን ያልነበረው ቢሆንም፣ አንድ ሰው ክህሎት፣ ተሰጥኦ እና በዘመኑ አለ የተባለው ትምህርት ሊኖረው እንደሚገባ ይታመናል፡፡

ስለ ሉቃስ ግለ ታሪክ የምናውቀው አራተኛ ነገር በሐዋርያት ሥራ ከተጠቀሱት አብዛኛ ምዕራፎች ውስጥ የጳውሎስ የአገልግሎት ባልደረባ የነበረ መሆኑ ነው፡፡

በፊሊሞና ቁር 24 ጳውሎ እንደገለፀው፣ ሉቃስ “አብሮ ሠራተኛ” ነበር፡፡ የሐዋርያት ሥራ 16፥6-10 እንደሚናገረው፣ ሉቃስ ጳውሎስን ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኘው በትራኦስ ሲሆን፣ ጳውሎ ወደ መቄዶኒያ እንዲሄድ ጥሪ ሲደርሰው አብሮት ነበር፡፡ ከዚህ አንፃር በሐዋርያት ሥራ 16፥40 - 20፥5 እንደተመዘገበው በፊልጵስዮስ ካደረገው የረጅም ጊዜ ቆይታ በስተቀር ሉቃስ ደጋግሞ ከጳውሎስ ጋር ነበረ፡፡ የሉቃስ ታማኝነት በተለይ የተመዘገበው፣ ጳውሎስ ወደ ሮም ባደረገው አሰቃቂ ጉዞ ወቅት ሲሆን በሐሥ 27፥1 ይገኛል፡፡

> **ከአዲስ ኪዳን ሰዎች ሁሉ፣ ሉቃስን ባገኘው እወዳለሁ፡፡ በአንድ ወቅት ሐኪም መሆንን ተመኝቼ ነበር፣ ስለዚህም እርሱ ዘወትር ይሰርቀኛል፡፡ እንዱን ወንጌል ለመጻፍ ብቁ የሚያደርጉት በርካታ ነገሮች ቢኖሩም፣ ይህኛው ግን ከእኔ አመለካከት ጋር እንደሚገጥም አስባለሁ፡፡ የመጀመሪያው የግሌ ነው፡፡ በሐዋርያት ሥራ 16 ውስጥ ሉቃስ “እኛ” ብሎ ይናገራል፡፡ በድንገት ራሱን በምስሉ ውስጥ ስገባዋል፤ ማለትም ከሌላ ሰው የሰማውን የሚያቀርብ ብቻ አይደለም ማለት ነው፡፡ ይልቁኑ እየተከናወነ ባለው ነገር ውስጥ ድርሻ ካላቸው ሰዎች አንዱ ይሆናል፣ ስለዚህም ቀደምቱን የክርስትና ሕይወት የማጣጣም ዕድል ነበረው ማለት ነው፡፡ እንደማስበውም ያ አስደናቂ ነገር ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ሐኪም የመሆኑ ነገር ነው፡፡ ያም ማለት እኔ ራሱ ላገኘው የምመኘው ስልጠና ሲሆን፣ ያ ዓይነቱ ሰው ነገሮች በውል መመርመራቸው ግድ የሚለው ሰው ነው፡፡ ኤችሁ ሐኪሞች ችብጦቻቸው አለመዛነፋቸውን፣ ዝርዝር መረጃዎቹ ትክክል መሆናቸውን ያረጋግጣሉ፣ ምክንያቱም ድምዳሜያቸው ለህመምተኛው መልካምን የሚያስገኝ ሊሆን ይገባዋልና ነው፡፡ ምናልባትም ስለ ሉቃስ እኔን የሚያስገርመኝ ሦተኛው ነገር በግሪኮ-ሮማዊው ግዛት ሲዘዋወር የነበረው አመለካከት ነው፡፡ በወንጌሉ ትረካ ውስጥ የነበረው አስተሳሰብ በእስራኤል ወይም በፓለስታይን ምድር ብቻ የተወሰነ አልነበረም፡፡ ዓለም አቀፋዊ አስተሳሰብ ነበረው፡፡ ዛሬ የክርስቲያን ወንጌል ዓለም አቀፋዊ ይዘት ሊኖረው ይገባል በምንልበት ወቅት፣ እውን የሆነ ግንዛቤ የሚያስጨብጠንን ነገር ከሉቃስ ወንጌል እናነባለን ምክንያቱም በግሪክ እና በሮም ደግሞም በተቀሩት የግሪኮ-ሮማዊ ግዛቶችም**

**ውስጥ የመዘዋወር ዕድል ነበረውና ነው፡፡ የኢየሱስ መልእክት በደረሰባቸው አካባቢዎች ሁሉ እንዴት ተዛማጅነት እንደነበረው የማስተዋል ዕድል ነበረው፡፡ (ዶ/ር ስቲቭ ሃርፐር)**

የሦስተኛውን ወንጌል ጸሐፊ ማንነት ከመረመርን፣ አሁን ደግሞ የሉቃስን ቀደምት ተደራሲያን ማንነት እንመልከት፡፡

## ቀደምት ተደራሲያን

የሉቃስን ቀደምት ተደራሲያን በሁለት መንገዶች እንመረምራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ መጽሐፉ ተነጥሎ ለቴዎፍሎስ መጻፉን እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ መጽሐፉ ሌላ ሰፋ ያለ ተደራሲ እንዳለውም እናያለን፡፡ እስኪ ቴዎፍሎስ የሉቃስ የመጀመሪያ አንባቢ ከመሆኑ እንጀምር፡፡

**ቴዎፍሎስ**

**በሉቃስ 1፥1-4 እና ደግሞም በሐዋርያት ሥራ 1፥1-2 የተጠቀሰው ሰው ቴዎፍሎስ ማን ነው? በሚለው ነገር ላይ ለበርካታ ምዕተ-ዓመታት ጠንካራ ሙግት ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ቴዎፍሎስ፣ "ቴዎፍሎስ" የሚለው ቃል ፍቺው "የእግዚአብሔር ወዳጅ" ማለት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ብዙዎች ቴዎፍሎስ አንድ የሆነ ሰው ሳይሆን፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉና የእግዚአብሔር ወዳጅ የሆኑ የሉቃስን አንባቢዎች ሁሉ የሚያካትት ቃል ነው ብለው ያስባሉ፡፡ ሌላኛው ዐቢይ አማራጭ ደግሞ፣ በእርግጥ ቴዎፍሎስ አንድ ግለሰብ ነበር የሚለው ነው፡፡ አብዛኞቹ ምሁራን፣ እኔም ተገቢ ነው ብዬ የምስማማበትን ሁለተኛውን አስተሳሰብ ይጨብጣሉ ምክንያቱም ሉቃስ "የከበርህ"፣ "kratista" ብሎ ይለዋልና ነው፡፡ ይህንኑ "kratista" የተሰኘውን ቃል የኋላ ኋላ ሉቃስ የሮም ባለሥልጣናት ለነበሩት ለፊሊክስና ለአክሪጳ ይጠቅሰዋል፡፡ እናም ሉቃስ የተጠቀመው ቃል አንድን ከፍተኛ ደረጃ ያለውን ሰው፣ እንዲያውም በሮም መንግሥት ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ የነበረውን ሰው በልቡናው ይዞ ነበር ማለት ነው፡፡ ከዚያም ባሻገር፣ ሉቃስ 1፥1-4 የመታሰቢያ ጽሑፍ ይመስላል፡፡ ከአብዛኛዎቹ የመታሰቢያ መግቢያ ጽሑፎች ዓይነት ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ታሪካዊ ሥራዎች አብዛኛውን ጊዜ ይህንን የመሰለውን መታሰቢያነት የሚሰጡት ድጋፍ ሰጪ ለሆነ፣ ማለትም ሥራው እንዲታተም ድጋፍ ለሚያደርግ ሰው ነው፡፡ እናም እንግዲህ፣ ይህ አጻጻፍ ከመታሰቢያነት ጽሑፍ ጋር በቀጥታ የሚጣጣም ስለሆነ በዚያም ምክንያት፣ እንዳልኩትም፣ በእርግጠኝነት ቴዎፍሎስ አንድ ሰው ነበር፡፡ (ዶ/ር ዴቪድ ባወር)**

የሉቃስ መቅድም ቴዎፍሎስ የእርሱ ደጋፊ፣ ማለትም አደራውን የሰጠውና የጽሑፍ ሥራውንም በገንዘብ የደገፈው መሆኑን ያመለክተናል፡፡ በሉቃስ 1፥1፣ ሉቃስ ሥራውን "የከበርህ ቴዎፍሎስ" በማለት ይጀምረዋል፣ ወይም ደግሞ "kratiste Theophile" ማለት ነው፡፡ "kratiste" የከፍተኛ አክብሮት መግለጫ ነው፡፡ እንዲያውም፣ በመላው አዲስ ኪዳን ውስጥ ይህ ቃል አገልግሎት ላይ የዋለው ሌሎች ሁለት ተጨማሪ ሰዎችን ለመግለጽ ብቻ ነው፡፡ እነርሱም የሮማ ገዢዎቹ ፊሊክስና ፊስጦስ ናቸው፡፡ ቴዎፍሎስ የሮሜ ከፍተኛ ባለሥልጣን ባይሆን እንኳን፣ በእርግጠኝነት በጣም የከበረና ታዋቂ መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡

በሉቃስና በቴዎፍሎስ መካከል ያለወ ግንኙነት ግን ከደጋፊነት የዘለለ ጥልቅ ነው፡፡ በአንድ በኩል፣ ቴዎፍሎስ የሉቃስ ተማሪ ነበር፡፡ በሉቃስ ፣፥3-4 ውስጥ፣ እንደዚህ እናነባለን፡

> ***የከበርህ ቴዎፍሎስ ሆይ፥... እኔ ደግሞ ስለ ተማርኸው ቃል እርግጡን እንድታውቅ በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትዬ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ። (ሉቃስ ፣፥3-4)***

ቴዎፍሎስ ስለ ኢየሱስ ያውቃል፡፡ ሉቃስ ግን ቴዎፍሎስ ስለ ተማረው ነገር የበለጠ እርግጠኛ እንዲሆን ስለፈለገ ይህንን የተሟላና ቅደም ተከተሉን የጠበቀ የኢየሱስ ሕይወት ታሪክ ጻፈለት፡፡

ሉቃስ የመጀመሪያ አንባቢው ቴዎፍሎስን ማድረጉን ከተመለከትን፣ ከዚያም ባሻገር ሉቃስ ሰፋ ያሉ ተደራሲያንም እንደነበሩት መመልከቱ ጠቃሚ ነው፡፡

## ሰፊው ተደራሲያን

ሉቃስ ለቴዎፍሎስ ብቻ ሳይሆን ሰፋ ላሉ ተደራሲያንም የጻፈ መሆኑን የምናስብባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡ አንደኛው ምክንያት፣ የቀደሙት ክርስቲያኖች ደብዳቤዎችንና ሌሎች ጽሑፎችን እየተቀባበሉ ወደ ማንበቡ ያዘነብሉ የነበረ መሆኑ ነው፡፡ አንዱን ለምሳሌ ብንጠቅስ፣ ጳውሎስ በቆላስይስ 4፥16 የጻፈውን አድምጡ፡

> **ይህችም መልእክት በእናንተ ዘንድ ከተነበበች በኋላ፥ በሎዶቅያ ሰዎች ማኅበር ደግሞ እንድትነበብ አድርጉ። ከሎዶቅያም የምትገኘውን መልእክት እናንተ ደግሞ አንብቡ። (ቆላስይስ 4፥16)**

ቀደምት ክርስቲያኖች ጽሁፎችን የሚለዋወጡ እስከ ሆነ ድረስ፣ ቴዎፍሎስም የሉቃስን መጽሐፍ በቶሎ ለሌሎች የማስተላለፍ ጉጉት እንደሚኖረው እሙን ነው፡፡

ከዚህም ባሻገር፣ የወንጌሉ ከፍተኛ ስነ-ጽሁፋዊ ባህርይ በሉቃስ ልቡና ውስጥ የሰፋ ተደራሲ ቀድሞውኑ የመኖሩን ነገር እርግጠኛ ያደርገዋል፡፡ የአጻጻፍ ዘይቤው ለአንድ ሰው እንደ ተጻፈ ግለሰባዊ ማስታወሻ ዓይነት ብቻ አይደለም፡፡ በሉቃስ ፣፥3 ውስጥ ሉቃስ ያጣቀሰው ሰፋ ያለ ታሪካዊ ምርመራ ሰፋ ያሉ ተደራሲያን መኖራቸውን ያመለክታል፡፡ ከዚህም በስቲያ፣ የወንጌሉና የሐዋርያት ሥራ ርዝማኔም የሚያመለክተን ሉቃስ ሰፋ ያሉ ተደራሲያንን ለመድረስ ትልቅ ሥራ የሠራ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ሰፊ ተደራሲ ግን ማን ነበር?

ሉቃስ በቀደምትነት የጻፈው ለአህዛብ ክርስቲያኖች ይመስላል፡፡ ለምሳሌ፣ የግሪክኛ አጣጣሉ ራሱ የአህዛብ ዓይነቱ ነው፡፡ ድነት ለአህዛብ ሁሉ ነው የሚል አፅንዖት ያነገበው የእግዚአብሔር መንግሥት ወንጌል ዓለም አቀፋዊ አቅርቦቱ ይህንን ያሳያል፡፡ እርግጥ ነው፣ የሉቃስ ወንጌል ለአይሁድ ክርስቲያኖችም ዋጋ ያለው ነው፡፡ ግን ልክ እንደ ማቴዎሱ ዓይነት በቀጥታ ለእነርሱ የተጻፈ አይደለም፡፡

በጥቅሉ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በጠቅላላ በየታሪክ ዘመናቱ ሁሉ በኖሩ ልጆቹ እንዲነበብና እንዲረዱት የእግዚአብሔር እቅዱ ነው፡፡ ሆኖም ጸሐፊዎች አንድን መጽሐፍ እንዲጽፉ መንፈስ ቅዱስ በሚነዳቸው ወቅት በእነርሱ ግላዊ ስብዕናና ፍላጎት አልፎ እንደሚሠራም ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ ተቀዳሚ እሳቤ፣ ሉቃስም ወንጌሉን ሲነድፍ ለቴዎፍሎስና ለመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ክርስቲያኖች ፍላጎት ቀጥተኛ ምላሽ መስጠትን አነጣጥሮ ነበር ማለት ነው፡፡ በአንፃሩ ደግሞ፣ ዘመነኛው ተደራሲ ደግሞ ሉቃስ ለእነርሱ በጻፈው በኩል ያደምጠዋል ማለት ነው፡፡ ሉቃስንና ቀደምት ተደራሲያኑን በልቡናችን ይዘን ወንጌሉን ስናነብብ፣ የጻፈውን ነገር በተሻለ መንገድ ለመረዳት ዝግጁ እንሆናለን በእኛም ሕይወት ተግባራዊ እናደርገዋለን፡፡

የወንጌሉን ጸሐፊ እና ተደራሲያን ማንነት ካወቅን፣ ወቅቱን ለመመርመር እንዘጋጃለን፡፡

# ወቅት

የሉቃስ ወንጌል የተጻፈበትን ወቅት በሁለት መንገድ እንመረምራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ የተቀናበረበትን ጊዜ እናስቀድማለን፡፡ ሁለተኛ፣ ሉቃስ የጻፈበትን ዓላማ እናያለን፡፡ የሉቃስ ወንጌል በተጻፈበት ወቅት እንጀምር፡፡

## ጊዜ

ጊዜው በ65 እና 67 ዓ.ም. መካከል ሊሆን እንደሚችል የሚያመለክቱ ቢያንስ ሁለት ምክንያቶች አሉ፡፡ በመጀመሪያ፣ በሉቃስ ወንጌልና በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ያሉት ንፅፅሮች ሉቃስ የማርቆስን ወንጌል አንዱ የምርምር ምንጩ እንዳደረገው በርካታ የአዲስ ኪዳን ምሁራን እንዲስማሙ አድርጓቸዋል፡፡ የማርቆስን ወንጌል ባየንበት ቀደም ባለው ትምህርታችን፣ የማርቆስ ወንጌል ቀደም ያለው ጊዜው 64ዓ.ም. ሊሆን እንደሚችል ድምዳሜ አድርገናል፡፡ ሉቃስ ማርቆስን በምንጭነት ከተጠቀመበት፣ ስለዚህ በጣም ቀደምት የሆነው ወቅት ሊሆን የሚችለው በ65ዓ.ም. አካባቢ ነው ማለት ነው፡፡

ሁለተኛ፣ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የተጻፈው በእርግጠኝነት ከ69ዓ.ም. በኋላ ሊሆን እንደማይችል ምናልባትም ከ67 ዓ.ም. በኋላ ሊሆንም እንደማይችል ይታሰባል፡፡ የሐዋርያት ሥራ ወሳኝ የሆኑ ክስተቶችን፣ ለምሳሌ በ65 ዓ.ም. አካባቢ ተፈጽሟል የሚባለውን የጳውሎስን መሰዋት፤ በ68ዓ.ም ያከተመውን የኔሮ ስደት፤ ወይም በ70ዓ.ም. የተፈፀመውን የኢየሩሳሌምን መውደቅ አልዘገበም፡፡ ይህ ትልልቅ ክስተቶችን ያለመዘገብ ነገር የሚያመለክተን ሉቃስ የጻፈው እነዚህ ነገሮች ከመከሰታቸው በፊት ነው፣ ወይም ቢያንስ ስለ እነርሱ ምንም ሳያውቅ መሆኑን ነው፡፡ የሐዋርያት ሥራ ፲፥፲ እንደሚናገረውም፣ የሉቃስ ወንጌል የሐዋርያት ሥራን ሳያጠናቅቅ በፊት መጻፉን ያመለክተናል፡፡ በእርግጠኝነት ግን በ69 ዓ.ም. ከኢየሩሳሌም መውደቅ በፊት አጠናቅቆታል፡፡

ሉቃስ የጻፈበትን ወቅት ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ወደ ዓላማው እንሻገር፡፡

**ዓላማ**

በሉቃስ ፲፥3-4 ውስጥ፣ ይህንን ወንጌል ለመጻፍ ምርመራ ያስፈለገበትን ምክንያት ሉቃስ እንዲህ ያስቀምጠዋል፡

> ***የከበርህ ቴዎፍሎስ ሆይ፥... እኔ ደግሞ ስለ ተማርኸው ቃል እርግጡን እንድታውቅ በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትዬ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ። (ሉቃስ ፲፥3-4)***

ሉቃስ ለቴዎፍሎስና እርሱን ለሚመስሉ አህዛብ ክርስቲያኖች ጻፈ፣ ዓላማውም በአይሁዳዊው መሲህ በኢየሱስ ያላቸውን ለጋ እምነት ማጠንከር ነበር፡፡

ሉቃስ ሲጽፍ፣ ቴዎፍሎስን የመሳሰሉ አህዛብ ክርስቲያኖች በእምነታቸው ጠንካራ ተግዳሮት ገጥሟቸው ነበር፡፡ እነዚህም ተግዳሮቶች ቢያንስ ከሁለት ምንጮች የመጡ ናቸው፡፡ በመጀመሪያ፣ ኔሮ በሮም በሚኖሩ ክርስቲያኖች ላይ ያስነሳው ስደት በግዛቱ ሁሉ ውስጥ ስደቱ ይስፋፋል የሚል ስጋት ፈጥሮ ነበር፡፡ ይህም ፍርሃት ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት አምጥቷል የሚለውን የክርስቲያኖች አዋጅ አንዳንድ ሰዎች እንዲጠራጠሩ አድርጓቸዋል፡፡

ሁለተኛ፣ አብዛኛው አይሁድ በሆነችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከአህዛብ ወገን በተለወጡት ክርስቲያኖች አቋም ላይ ክርስቲያኖች ክርክር ነበራቸው፡፡ ይህ አግባብ ያልሆነ ጥላቻባ መከፋፈል ኢየሱስ ለሰው ዘር በሙሉ ድነትን ሰጥቷል የሚለው ሃሳብ ጥርጣሬን ፈጥሯል፡፡

ለነዚህ ተግዳሮቶችና ጥርጣሬዎች ምላሽ ይሆን ዘንድ፣ እና አሃዛብ አማኞች ኢየሱስን ለመከተል በመምረጣቸው ትክክለኛ ምርጫን እንዳደረጉ ሊያረጋግጥላቸው ሉቃስ ጻፈ፡፡ ኢየሱስ በእውነት የእግዚአብሔርን መንግሥት አውጇል፡፡ አህዛብ ክርስቲያኖችም የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት ናቸው፡፡ ለኢየሱስ ታማኝ ሆነው ከዘለቁ፣ የድነትን በረከት ሁሉ እንደሚቀበሉ እርግጠኛ ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡

የሉቃስን ወንጌል ዳራ ከመረመርን፣ ውቅሩንና ይዘቱን ወደ ምንመለከትበት ሁለተኛ ዐቢይ ርዕሳችን እንሸጋገር፡፡

# ውቅርና ይዘት

ቀደም ብለን ከተመለከትናቸውና በዚህ ተከታታይ ትምህርታችን ከቀረቡት እንደምታስታውሱት፣ ተለቅ ባለው ዕይታ አራቱም ወንጌላት የኢየሱስን ሕይወት በቅደም ተከተል ያቀርቡልናል፡፡ ግን አነስ ባለው ዕይታ ደግሞ፣ ስለ ኢየሱስ የሚጽፏቸውን ታሪኮች በተለያዩ መርሆች ያቀናጁቸዋል፡፡ ለምሳሌ፣ ማቴዎስና ማርቆስ አንዳንድ ጊዜ ጽሑፎቻቸውን በተለያዩ መሪ ሃሳቦች መሠረት ይሰድሯቸዋል፡፡ በንጽጽር ግን፣ ሉቃስ የወንጌሉን አብዛኛወን ክፍል ያደራጀው በመልክዓ ምድር አንጻር ነው፡፡

በዚህ ትምህርት ላለን ዓላማ፣ የሉቃስን ወንጌል በስድስት ክፍሎች እንከፍለዋለን፡ ከ1፥1-4 ያለው አጭር መቅድም፣ ሌሎች አምስት ዐበይት የታሪክ ጎራዎችን ያስከትላል፡፡

- የወንጌሉ የመጀመሪ ዐቢይ ክፍል የኢሱስን ጅማሬ የሚገልፀውና በይሁዳ አውራጃና በዮርዳኖስ ወንዝ ላይ የሚያተኩረው ነው፡፡ ይህ ክፍል ከ1፥5 - 4፥13 ይዘልቃል፡፡
- ሁለተኛው ዐቢይ ክፍል በገሊላ የኢየሱስ አገልግሎት ላይ የቐረበው ትረካ ሲሆን ከ4፥14 -9፥50 ይዘልቃል፡፡
- ሦስተኛው ዐቢይ ክፍል በ9፥51-19፥27 የሚዘልቀው ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገውን ጉዞ የሚዘግበው ነው፡፡
- አራተኛው ዐቢይ ክፍል በኢየሱስ የኢየሩሳሌምና አቅራቢያዋ አገልግሎት ላይ የሚያተኩረው በ19፥28-21፥38 የሚገኘው ነው፡፡
- በመጨረሻ፣ አምስተኛው የሉቃስ ወንጌል ዐቢይ ክፍል ከኢየሩሳሌም ውጪ በኢየሡስ መሰቀልና ትንሣኤ ላይ የሚተርከው በ22፥1-24፥53 የሚገኘው ነው፡፡

የሉቃስን ወንጌል መቅድም እስከተመለከትን ድረስ፣ በአምስቱ ዐቢይ የትረካ ክፍሎቹ ላይ እናተኩራለን፣ በሉቃስ 1፥5-4፥13 ከሚገኘው ከኢየሱስ ጅማሬ እንነሳለን፡፡

# የኢየሱስ ጅማሬ

ስለ ኢየሱስ ጅማሬ ሉቃስ የጻፈው የሚጀምረው ከኢየሱስ ልደት ቀደም ብሎ ይሆንና ከአደባባይ አገልግሎቱ ቀደም ብሎ ያለውን ሕይወቱን ሁሉ ይዳስሳል፡፡

በእነዚህ ምዕራፎች ሉቃስ ማሳየት የወደደው ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ደግሞም የዳዊት ልጅ መሆኑን ማለትም ፍፁም መለኮትና ፍፁም ሰው መሆኑን ነው፡፡ ከዳዊት ልጅነቱ ይበልጥም፣ ኢየሱስ መሲህ ወይም ክርስቶስ፣ ማለትም የእግዚአብሔርን መንግሥት ወደ ምድር በማምጣት ለዓለም ሁሉ ድነትን የሚያስገኝ ነው፡፡

በዚህ ትረካ ከጫፍ እስከ ጫፍ፣ የብሉይ ኪዳንን የእግዚአብሔር ተስፋዎች ሉቃስ ደጋግሞ ይጠቅሳል፣ ያንንም እግዚአብሔር እነዚህን ተስፋዎች በኢየሱስ አማካይነት የፈፀማቸው መሆኑን ለማመልከት ይጠቀምበታል፡፡ ስለዚህም፣ ለእግዚአብሔር ታማኝ ለመሆንና የመንግሥቱን የበረከት ተስፋዎች ለመቀበል ኢየሱስን እንደ ንጉሥና አዳኝ መቀበል ያስፈልጋል፡፡

እነዚህ ምዕራፎች በአራት ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ፡ የመጥምቁ ዮሐንስና የኢሱስ መወለድ አዋጅ፤ ተዛማጅ ልደቶቻቸውና የልጅነት ጊዜዎቻቸው፤ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ የሠጠው መግለጫ፤ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ የመሆኑ ሁለት ማረጋገጫዎች ናቸው፡፡ በሉቃስ 1፥5-5ለ በሚገኘው በልደታቸው አዋጅ እንጀምር፡፡

## የልደታቸው መታወጅ

ሉቃስ ወንጌሉን በመልአኩ ገብርኤል መገለጥ መክፈቱ ወሳኝነት አለው፡፡ ከመቶ ዓመታት ቀደም ብሎ፣ መልአኩ ገብርኤል የእስራኤል ምርኮ 400 ዓመታት እንደሚቆይ ማወጁን ዳንኤል ምዕራፍ 9 ይገልጥልናል፡፡ በእግዚአብሔር ፍርድ ስር በነበሩባቸው ረጅም ዓመታት፣ እስራኤል በእስራት ውስጥ ነበረች፡፡ በሉቃስ ወንጌል ግን፣ መልአኩ ገብርኤል የፍርድ ዘመን ማብቃቱን አውጇል፡፡

በሉቃስ ፩፥5-25፣ ገብርኤል የመጥምቁ ዮሐንስን መወለድ አስቀድሞ ተናግሯል፡፡ መልአኩ ገብርኤል በይሁዳ ወደሚኖረው ወደ ካህኑ ዘካርያስ በመምጣት መካኒቱ ሚስቱ ኤልሳቤጥ በተዓምራት ወንድ ልጅ እንደምትወልድ፣ ስሙንም ዮሐንስ እንደሚለው ነገረው፡፡ ከመወለዱ ጀምሮም በመንፈስ ቅዱስ ይሞላል፣ የእግዚአብሔርንም የመዳን መንገድ ለማዘጋጀት በታላቁ ነቢይ በኤልያስ መንፈስም ያገለግላል፡፡ በመጀመሪያ፣ ዘካርያስ የመልአኩን መልእክት ተጠራጠረ፣ እናም ልጁ እስኪወለድ ድረስ ዲዳ ሆነ፡፡

ሉቃስ የዮሐንስ መወለድ የታወጀበትን የገብርኤልን አዋጅ በሉቃስ ፩፥26-28 ከታወጀው ከትልቁ የኢየሱስ ልደት አዋጅ ጋር በጣምራ ያቀርበዋል፡፡ እግዚአብሔር በተዓምር ወንድ ልጅ በማህፀኗ እንደሚያስቀምጥ፣ እግዚአብሔርም የልጁ አባት እንደሚሆን ገብርኤል ለማርያም ነገራት፡፡ የእግዚአብሔርም ልጅ ስሙ ኢየሱስ ሲሆን፣ ትርጓሜውም "**አዳኝ**" ማለት ነው፡፡ ከዚያ ባሻገር፣ የዳዊትን ዙፋን እንደሚወርስ፣ ያም ማለት የእግዚአብሔርን መንግሥት ማዳን ወደ ምድር የሚያመጣ መሲህ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ማርያምና ኤልሳቤጥ ዘመዳሞች ስለነበሩ፣ በይሁዳ የምትኖረውን ኤልሳቤጥን በመጎብኘት የእግዚአብሔርን ልጅ የፀነሰች መሆኗን ነገረቻት፡፡ ስለዚህ ጉብኝት በሉቃስ ፩፥39-56 እናነባለን፡፡ ማርያም ኤልሳቤጥን ሰላም ባለቻት ወቅት፣ ዮሐንስ በእናቱ ማኅፀን ውስጥ በደስታ ዘለለ፣ እናም ኤልሳቤጥ ወዲያውኑ በመንፈስ ቅዱስ ተሞላች ስለዚህም የልጇን አፀፋዊ ምላሽ ወሳኝነት ተረዳች፡፡ ኤልሳቤጥም ማርያምን ባረከቻት፣ የማርያምንም ልጅ ጌታዬ አለችው፡፡ ማርያምም በምላሹ፣ ፀሎተ ማርያም ተብሎ የሚጠራውን እና በሉቃስ ፩፥46-55 የሚገኘውን ደግሞም በልጇ በኩል ስለሚመጣው ድነት የተሰማትን ትልቅ ደስታ የገለጠችበትን ታዋቂ የምሥጋና መዝሙሯን ዘመረች፡፡

የልደታቸውን አዋጅ በማስከተል፣ ሉቃስ የዮሐንስንና የኢየሱስን ልደትና የልጅነት ጊዜያቸውን በሉቃስ ፩፥57-2፥52 በማነፃፀር ያቀርባል፡፡

## ልደታቸውና የልጅነት ጊዜያቸው

ሉቃስ የዮሐንስን ልደትና የልጅነት ጊዜ የዘገበው በሉቃስ ፩፥57-80 ውስጥ ነው፡፡ ዮሐንስ የተወለደው ዕድሜያቸው ከገፋ ወላጆች ነው፡፡ በስምንተኛውም ቀን ሊያስገርዙት ወደ ቤተመቅደስ ሲወስዱት፣ የአባቱ ድምፅ ተፈታ፡፡ በዚያን ጊዜ፣ ዘካርያስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ልጁ የትልቁን የዳዊትን ልጅ፣ የመሲሁን መንገድ የሚያዘጋጅ መሆኑን ትንቢት ተናገረ፡፡

በሉቃስ ፥69-70 የመሲሁን ሚና ዘካርያስ እንዴት እንደገለጠው አድምጡ፡

> ***ከጥንት ጀምሮ በነበሩት በቅዱሳን ነቢያት አፍ እንደ ተናገረ፥ በብላቴናው በዳዊት ቤት የመዳን ቀንድን አስነስቶልናል፤***
> ***ማዳኑም ከወደረኞቻችንና ከሚጠሉን ሁሉ እጅ ነው፤***
> ***እንደዚህ ለአባቶቻችን ምሕረት አደረገ፤ ለአባታችን ለአብርሃምም የማለውን መሐላውን ቅዱሱን ኪዳን አሰበ፤***
> ***በእርሱም ከጠላቶቻችን እጅ ድነን በዘመናችን ሁሉ ያለ ፍርሃት በቅድስናና በጽድቅ በፊቱ እንድናገለግለው ሰጠን።***
> ***ደግሞም አንተ ሕፃን ሆይ፥ የልዑል ነቢይ ትባላለህ፥ መንገዱን ልትጠርግ በጌታ ፊት ትሄዳለህና፤ (ሉቃስ ፥69-76)***

በብሉይ ኪዳን፣ እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዳዊት የድነትን የቃል ኪዳን ተስፋ ሰጣቸው፡፡ ዘካርያስም እግዚአብሔር ያንን ቃል ኪዳን ሊፈፅም ዘመኑ እንደደረሰና ልጁ ዮሐንስ፣ መንገዱን የሚጠርግ ነቢይ መሆኑን ተነበየ፡፡

አጥሎ ደግሞ፣ በሉቃስ 2፥1-52 ውስጥ፣ የኢየሱስን ልደትና የልጅነት ወቅት ሉቃስ ይዘግብልናል፡፡ በዚህ ዘገባና ቀደም ብሎ ስለ ዮሐንስ ልደት ባሰፈረው ዘገባ መካከል በርካታ ጉድኝት ያለ ሲሆን፣ ሉቃስ በኢየሱስ ልደትና የልጅነት ወቅት ላይ ያቀረበው ዘገባ ረዘም ያለና ይበልጥ የተስፋፋ ነው፡፡ የሚጀምረውም ኢየሱስ በዳዊት ከተማ፣ በይሁዳዋ ቤተልሔም ስለ መወለዱ በሚናገረው በሉቃስ 2፥1-20 ነው፡፡

የኢየሱስ ልደት ትኅትና የሞላበት ነው፡፡ የተወለደው በበረት ሲሆን የተኛውም በከብቶች ግርግም ነበር፡፡ በአካባቢው ለነበሩ እረኞች በመላእክት የተነገረው የመወለዱ የምሥራች ግን ግርማዊነትን የተላበሰ ነበር፡፡ በሉቃስ 2፥10-11 መልአኩ ለእረኞቹ የነገራቸውን አድምጡ፡

> ***መልአኩም እንዲህ አላቸው፦ እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ፤***
> ***ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና።***
> ***(ሉቃስ 2፥10-11)***

መልአኩ ያወጀው መልካሙን የምሥራች ወይም "**ወንጌል**" ሲሆን ያም መሲሁ ንጉሥ የእግዚአብሔርን ህዝብ ከእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚያድናቸው የሚያበስር ነው፡፡

ይህ የተላከ መልአክ ስለ ኢየሱስ መወለድ እግዚአብሔርን በሚያመሰግኑ የሰማይ ሠራዊት ታጀበ፡፡ ምንም እንኳን የማርያም ልጅ የኢየሱስ ልደት ትሑት ቢሆንም፣ በእርግጥ የተመረጠው መሲህና ንጉሥ ነው የሚለውን ሉቃስ ግልፅ ያደርገዋል፡፡

ቀጥሎም፣ ሉቃስ በ2፥21-40 ውስጥ ስለ ኢየሱስ መገረዝናበኢየሩሳሌም መቅደስ ስለ መሰጠቱ ያብራራል፡፡ በመቅደስ ውስጥ፣ መንፈስ ቅዱስ ስምዖንን ደግሞም ቅድስቲቱን ነቢይት ሃናን

በመሙላት ኢየሱስ መሲሁ ለዓለምም ድነትን የሚያመጣ መሆኑን እንዲያውቁ አደረገ፡፡ በሉቃስ 2፥30-32 ስምዖን ለእግዚአብሔር ያቀረበውን ምሥጋና እስኪ አድምጡ፡

*ዓይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና፤*
*ይህም ለአሕዛብ ሁሉን የሚገልጥ ብርሃን ለሕዝብህም ለእስራኤል ክብር ነው።*
*(ሉቃስ 2፥30-32)*

ይህም እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ የተናገረበት፣ የኢሳያስ 49፥6 ፍፃሜ ነበር፡

*እርሱም፦ የያዕቆብን ነገዶች እንድታስነሣ ከእስራኤልም የዳኑትን እንድትመስል ባሪያዬ ትሆን ዘንድ እጅግ ቀላል ነገር ነውና እስከ ምድር ዳር ድረስ መድኃኒት ትሆን ዘንድ ለአሕዛብ ብርሃን አድርጌ ሰጥቼሃለሁ ይላል። (ኢሳያስ 49፥6)*

ኢየሱስ ለእስራኤል ክብርና ድነትን የሚያመጣ መሲህ መሆኑን እግዚአብሔር በስምዕን በኩል ገለጠ፡፡ ከዚህም በበለጠ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል ለአህዛብ መንግሥታት እንደሚሰጥ እና እነርሱም እንደሚድኑ ይናገራል፡፡

በመጨረሻም፣ በሉቃስ 2፥41-52 በተጠቀሰ አጭር ታሪክ በመቅደስ ወደተገለጠው ወደ ኢየሱስ ልጅነት ሉቃስ መለስ ይላል፡፡ ኢየሱስ ዐሥራ ሁለት ዓመት ሲሞላው፣ በኢየሩሳሌም የፋሲካን በዓል ለማክበር ከወላጆቹ ጋር ወጣ፣ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ግን ከእነርሱ ተለየ፡፡ ወላጆቹም ከቀናት በኋላ በቤተመቅደስ ሸንጎ ውስጥ ከመምህራን ጋር ሲነጋገር አገኙት፡፡ በመቅደስ የነበረ ሰው ሁሉ በኢየሱስ እውቀትና መረዳት ይደነቅ ነበር፡፡

ማርያም ኢየሱስን ባናገረችው ወቅት፣ የሰጣት መልስ እርሱ ልዩ መሆኑን ገለጠ፡፡ በሉቃስ 2፥49 ኢየሱስ ለማርያም የነገራትን አድምጡ፡-

*በአባቴ ቤት እሆን ዘንድ እንዲገባኝ አላወቃችሁምን? (ሉቃስ 2፥49)*

ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ መቅደሱ የአባቱ ቤት ነበር፡፡

የዮሐንስንና የኢየሱስን ልደትና የልጅነት ወቅት አስከትሎ፣ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ በሉቃስ 3፥1-20 የተናገረውን ሉቃስ ይዘግባል፡፡

## ዮሐንስ ኢየሱስን ያመሳሰለበት መንገድ

በዚህ ትረካ ውስጥ፣ ዮሐንስ ኢየሱስን በቀጥታ ከመሲሁ ጋር በማመሳሰል የእግዚአብሔርን የማዳን መንገድ ጠራጊ ሆኖ ተገልጧል፡፡ በዮርዳኖስ ወንዝ አካባቢ በሰጠው የስብከት አገልግሎቱ፣ ዮሐንስ የምትመጣውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ያውጅ፣ ሰዎች ከኃጢአታቸው እንዲመለሱ ያስጠነቅቅ እና ንስሓ የሚገቡትን ያጠምቅ ነበር፡፡ ኢየሱስ ሊጠመቅ ወደ እርሱ ሲመጣ ግን፣ ዮሐንስ በቀጥታ ከመሲሁ ጋር በማገናኘት እና ያለማወላወልም የመሲሁን የጫማ ማሰሪያ እንኳን ለመፍታ ብቁ

እንዳልሆነ ያውጅ ነበር፡፡ በኢሳያስ 44፥3 እና በሕዝቅኤል 39፥29 እንደ ተነገረው የብሉይ ኪዳን ትንቢት፣ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚያጠምቅ ዮሐንስ ይናገር ነበር፡፡ ይህም የታሪክ የመጨረሻው ዘመን መቃረቡን፣ የዕግዚአብሔርም ማዳን በሙላት መገለጡን የሚያሳይ ነው፡፡

> **በዚህ ስፍራ በዘፀአት 19፣ እስራኤላውያን ከእግዚአብሔር ሊሰሙ በተቃረቡበት ወቅት ወይም እግዚአብሔር በሲና ተራራ ሊወርድ በነበረበት ወቅት፣ ልብሳቸውን እንዲያጥቡና ራሳቸውን እንዲያነፁ የተነገራቸው መሆኑን መጥቀስ ደስ ያሰኛል፡፡ እናም፣ የመንፃቱ ነገር የሚያሳየን ሰዎች ለእግዚአብሔር መምጣት ወይም ለእግዚአብሔር መገለጥ ራሳቸውን ሊያዘጋጁ የሚገባ መሆኑን ነው፡፡ የመጥምቁ ዮሐንስንም አዋጅ በምንመለከትበት ወቅት፣ በመሠረታዊነት የጠናገረው እግዚአብሔር በፍርድ ሊመጣ ስለሆነ ሰዎች ራሳቸውን በንስሓ ሊያዘጋጁ እንደሚገባ እና ከዚም ሊጠመቁ እንደሚገባ ነው፡፡ (ዶ/ር ዴቪድ ሬድሊንግሰ)**

> **በወንጌላት ውስጥ፣ ዮሐንስ ሰዎችን ሲያጠምቅ እናገኘዋለን፡፡ ከዚያም ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ሲመጣ እናገኘዋለን፡፡ ለምን ይሄን አደረገ? ማለቴም፣ ዮሐንስ ንስሓ ግቡ ለእግዚአብሔርም መንግሥት ተዘጋጁ፣ ነበር የሚለው፡፡ ታዲያ ኢየሱስ ንስሓ ሊገባ ይገባዋልን? እንደማያስፈልገው ግልፅ ነው፡፡ እርሱ ያለ ኃጢአት የሆነው የእግዚአብሐየር ልጅ ነው፡፡ ታዲያ ለምን በዮሐንስ ተጠመቀ? እንግዲህ፣ የዮሐንስ ጥምቀት ለምትመጣዋ የእግዚአብሔር መንግሥት መዘጋጃ እንደነበር መገንዘቡ ወሳኝ ነው፡፡ ከክርስቲያኑ ጥምቀት ጋር የሚመሳሰል ስላልነበረ ሰዎችን ንስሓ እንዲገቡ፣ እንዲያምኑ ሲጣራ የእግዚአብሔር መንግሥት እየመጣች ነው፤ ንጉሡም መጥቷል፣ ብሎ እያበሰረ ነበር፡፡ ስለዚህም ሰዎች ራሳቸውን ለዚያ ያዘጋጁ ነበር፡፡ ኢየሱስ፣ በዮሐንስ ሊጠመቅ ሲመጣ፣ አገልግሎቱን ሊጀምር ነበር፡፡ በሁሉም ወንጌላት ውስጥ ጥምቀቶቹ የጀመሩት በኢየሱስ አገልግሎት ጅማሬ ላይ ነበር፡፡ እርሱ ራሱን ከእኛ ጋር እያመሳሰለ ነበር፡፡ እስኪ ማቴዎስ ያስቀመጠበትን መንገድ አስቡት፣ ጽድቅን ሁሉ መፈፀም፡፡ ስለዚህ እርሱ ንስሓ ሊገባ ስለሚያስፈልገው አልነበረም፡፡ ኃጢአተኛም ስለነበረ አይደለም፡፡ እርሱ ከህዝቡ ጋር ሊመሳሰል ስለወደደ ነው፡፡ ከዚያም የአደባባይ አገልግሎቱን ጀመረ፡፡ በሕወቱ ሁሉ እኛን ወክሎ የሚደርገውን ሁሉ አደረገ፣ በሞቱ፣ በትንሣኤውና በዕርገቱም ወደ ድምዳሜ አመጣው፡፡ ስለዚህም፣ መጥቶ በዮሐንስ የተጠመቀው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ በአንድ ጎኑ አገልግሎቱን በይፋ ሊጀምር፣ ሊሠራ ያለውን ለመጀመር፣ ዮሐንስ ወደፊት ይመጣል ይል የነበረው በእርሱ እንደመጣ ለማወጅ ነበር፡፡ እርሱ አሁን መንግሥቱን አምጥቷል፡፡ (ዶ/ር ስቴፈን ዌሉም)**

ዮሐንስ ኢየሱስን ያመሳሰለበትን ሁኔታ ከተመለከትን፣ የዚህ ትረካ የመጨረሻ ክፍል ወደ ሆነው ወደ አራተኛው ክፍል እንሸጋገር፡፡ ይህም በሉቃስ 3፥21 - 4፥13 ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ የተረጋገጠበት ነው፡፡

**የእግዚአብሔር ልጅነቱ መረጋገጡ**

ሉቃስ የኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅነት ለማረጋገጥ ሦስት የተለያዩ ማረጋገጫዎችን ያቀርብልናል፣ የሚጀምረውም በሉቃስ 3፥21-22 በተመዘገበው መለኮታዊ ማረጋገጫ ነው፡፡ እስኪ ይህንን በሉቃስ 3፥22 የተመዘገበ የኢየሱስ የጥምቀት ወቅት መግለጫ አድምጡ፡

> ***መንፈስ ቅዱስም በአካል መልክ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ወረደ፤ የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፥ በአንተ ደስ ይለኛል የሚል ድምፅም ከሰማይ መጣ። (ሉቃስ 3፥22)***

በኢየሱስ ጥምቀት ወቅት፣ ኢየሱስ ልጁ መሆኑን እግዚአብሔር ራሱ ገሃድ በሆነ የመንፈሱ መገለጥና ከሰማይ በመጣ ድምፅ አረጋገጠ፡፡

በመቀጠልም፣ በሉቃስ 3፥23-38 ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የዝርሐረግ ማስረጃ ሉቃስ ያቀርባል፡፡

እንደ ማቴዎስ ሁሉ፣ ሉቃስም የኢየሱስን የትውልድ ሐረግ ከዳዊትና ከአብርሃም የጽድቅ ዘር ጋር ያገናኘዋል፡፡ ከማቴዎስ ለየት አድርጎ ግን፣ ሉቃስ የሰውን ዘር የጽድቅ ዘር እስከ አዳም ድረስ እንዲዘልቅ ያደርገዋል፡፡ የዚህን የዘር ሐረግ ቆጠራ ወሳኝነት ለመገንዘብ፣ በሉቃስ 3፥38 የተጠናቀቀበትን መንገድ አድምጡ፡

> ***… የሴት ልጅ፥ የአዳም ልጅ፥ የእግዚአብሔር ልጅ። (ሉቃስ 3፥38)***

ሉቃስ አዳምን "የእግዚአብሔር ልጅ" ይለዋል፡፡ በእነዚህ ምዕራፎች ሁሉ ተመሳሳይ የሆነው ስም ለኢየሱስ ተሰጥቷል፡፡ በዚህ መንገድ፣ ሌሎች የአዲስ ኪዳን ክፍሎች በግልጽ የሚያስተምሩትን አንድ ነገር ሉቃስ ይጠቁመናል፡፡ እንደ እግዚአብሔር ልጅ፣ ኢየሱስ የመጀመሪያውን የእግዚአብሔርን ልጅ፣ የአዳምን፣ ዓላማ ለማሳካት የቆረጠ ነበር፡፡ ወይም ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 15፥45 እንዳስቀመጠው፣ ኢየሱስ "የኋለኛው አዳም" ነው፡፡ አዳም በምድር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሊያገለግል በምድር የተሾመ አገልጋይ ንጉሥ ነበር፡፡ ሆኖም በአሳዛኝ ሁኔታ ወደቀ፡፡ ኢየሱስ ግን የአዳምን ውድቀት ለማስወገድ የተገለጠ ትልቅ የእግዚአብሔር ልጅ ሲሆን፣ በዚህም ድነትን ለዓለም ህዝብ ሁሉ አመጣ፡፡

የመጨረሻው የኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅነት ማረጋገጫ ኢየሱስ ራሱ በሉቃስ 4፥1-13 የሰጠው ማረጋገጫ ነው፡፡

ይህም ኢየሡስ በምድረ በዳ የተፈተነበት ታሪክ ነው፡፡ ሉቃስ በ4፥1 ላይ እንደጠቀሰው፣ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ወደ ምድረ በዳ ተወሰደ፣ በዚያም በሰይጣን ተፈተነ፡፡ ዲያቢሎስም ኢየሱስን ድንጋዩን ዳቦ እንዲያደርግ፣ በመንግሥታትም ላይ ሥልጣንን ከዲያቢሎስ እንዲቀበል እና ከመቅደስም ጫፍ ራሱን ወደ መሬት እንዲወረውር ፈተነው፡፡ ዲያቢሎስም ከእነዚህ ሁለቱን ፈተናዎች የጀመረው "የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክስ" በሚል የማንጓጠጥ ቃል ነው፡፡ በምላሹም፣

ኢየሱስ ሦስቱንም የሰይጣን ፈተናዎች በብርቱ በመቃወም እና ታማኝ የሆነ የእግዚአብሔር ልጅ ሊያደርግ እንደሚገባውም ከብሉይ ኪዳን በመጥቀስ ድል አደረገው፡፡

> **ኢየሱስ በምድረ በዳ በሰይጣን ሲፈተን ከመጽሐፍ ቅዱስ የጠቀሰው በበርካታ ምክንያቶች ነው፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ የወንጌላት ጸሐፊዎች ያደረጉት ኢየሱስን እንደ እግዚአብሔር ልጅ መሳል ወይም መግለጥ ነው፡፡ እናም ስለዚህ፣ ከቅዱሳት መጻሕፍት ሲጠቅስ የምናየው ከእግዚአብሔር ጋር ባለው የቃል ኪዳን ግንኙነት ምክንያት ነው፡፡ ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት በመሄድ ስለ እርሱ ቃል ኪዳናዊ ግንኙነት ከተነገሩት የሚጠቅሰው ነገሮችን በሥርዓቱ ለመምራት፣ የእርሱም ሥልጣን ከእግዚአብሔር አብ ጋር ካለው ግንኙነት አንፃር በአግባቡ እንዲታይ እና የዲያቢሎስም የሥልጣን ውሱንነት እንዲገለጥም ነው፡፡ እናም ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም በማለት ሲናገር ላለው ቃል ኪዳናዊ ግንኙነት የሚሰጠውን ቅድሚያ እያሰበና ከዲያቢሎስ የደረሰበትን ፈተና ሲቃወም እንዲያግዘውም ነው፡፡ ሆኖም በቀጥታ የጠቀሰው በዘዳግም 6 እስከ 8 ከተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ በዚያ ስፍራ ሙሴ የሚናገረው የእግዚአብሔር ሕዝብ በምድረ በዳ ስለገጠመው ልምምድ ነው፡፡ ያም የዘፀአቱ ህዝብ የምድረ በዳ ልምምድ፣ በህዝቡ ልብ ውስጥ የነበረውን ለመፈተንና በልቡ ያለውን ለማየት ነበር፡፡ በዚህም ሲሆን የምናየው ተመሳሳዩ ነው፡፡ በኢየሱስ ፈተና ልጅነቱ ተፈተሸ፣ እስራኤል ፈተናውን ሲወድቅ፣ ኢየሱስ ግን ፈተናውን አለፈ፡፡ በዚህ የፈተና ትረካ ውስጥ በወንጌላት ጸሀፊዎችና በኢየሱስ በራሱም ስለ ብሉይ ኪዳን ጽሑፎች አጠቃቀም በንፅፅር እንመለከታለን፡፡ (ዶ/ር ግሬግ ፔሪ)**

አዳምን የእግዚአብሔር ልጅ በማድረግ የሚደመደመውን የዘር ሐረግ ቆጠራ ተከትሎ የመጣ በመሆኑ፣ ሉቃስ ስለ ኢየሱስ መፈተን ያቀረበው ዘገባ ሊታይ የሚገባው አዳም በዘፍጥረት 3 ከገጠመው ፈተና ጋር በተቃርኖ ነው፡፡ በዚያ ታሪክ ውስጥ፣ ዲያቢሎስ በኤድን ገነት አዳምን ፈተነው፣ አዳምም ወደቀ፣ ስለዚህም እግዚአብሔር ፍጥረትን ረገመ የሰውንም ዘር በጠቅላላ ወደ ምድረ በዳ አባረረ፡፡ በተቃርኖው ግን፣ ኢየሱስ በምድረ በዳ ፈተናውን ተቋቋመ፣ ይህም እርሱ በእውነት የታመነው የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑንና የእግዚአብሔርንም የታመነ ህዝብ ወደ መንግሥተ ሰማይ የሚመለስ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

በይሁዳና በዮርዳኖስ አካባቢ የኢየሱስን ጅማሬ ከተመለከትን በኋላ የሚመጣው ቀጣዩ ዐቢይ የሉቃስ ወንጌል ክፍል በገሊላ የኢየሱስን አገልግሎት የሚዘግበው ነው፡፡ ይህም ክፍል ከ 4፥14-9፥50 ይዘልቃል፡፡

## በገሊላ የኢየሱስ አገልግሎት

በወንጌሉ በዚህኛው ክፍል ውስጥ፣ ሉቃስ የኢየሱስን ተዓምራዊ ኃይልና የወንጌል ስብከት በርካታ ምሳሌዎችን ዘግቧል፣ ይህንንም ያደረገው ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን በተስፋ የተነገረለት በመንፈስ የተቀባው አዳኝ መሆኑን ለማረጋገጥ ነበር፡፡

በገሊላ የኢየሱስን አገልግሎት የዳሰሰው የሉቃስ ትረካ በአምስት ክፍሎች ይከፈላል፡ በመጀመሪያ፣ በናዝሬት የኢየሱስ ስብከት፤ ሁለተኛ፣ ትምህርቱና ተዓምራቱ፤ ሦስተኛ፣ በኢየሱስና በመጥምቁ

ዮሐንስ ሃላፊነቶች መካከል ያሉ ልዩነቶች፤ አራተኛ፣ የኢየሱስ ተጨማሪ ትምህርቶችና ተዓምራቶች፤ አምስተኛ፣ ኢየሱስ ዐሥራሁለቱን ደቀመዛሙርት ለአገልግሎት ማዘጋጀቱ ናቸው፡፡ አስቀድመን በሉቃስ 4፥14-30 በተመዘገበው በኢየሱስ የናዝሬት ስብከት እንጀምርና ሁሉንም በየተራ እንመለከታቸዋለን፡፡

## የናዝሬቱ ስብከት

ሦስቱም ተመሳሳይ ወንጌላት በኢየሱስ ተዓምራዊ የኃይልና የወንጌል አዋጆች ላይ ያተኮሩት በገሊላ አገልግሎቱ ወቅት ላይ ነው፡፡ የሉቃስ አቀራረብ ግን ከሌሎቹ የተለየና በገዛ ከተማው በናዝሬት የሰጠውን የመጀመሪ ስብከቱን በዚህ ደረጃ በማስተዋወቅ የሚጀምር ነው፡፡ ኢየሱስ በሰንበት ቀን በምኩራብ እንደተገኘና የኢሳያስን መጽሀፍ ጥቅልል እንደሰጡት ሉቃስ ዘግቧል፡፡ ስለዚህ፣ እርሱም ኢሳያስ 61፥1-2 አነበበና አንድ አስደናቂ አዋጅ አወጀ፡፡ እስኪ ኢየሱስ በሉቃስ 4፥18-21 ያነበበውን አድምጡ፡

> ***የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፥ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል … ዛሬ ይህ መጽሐፍ በጆሮአችሁ ተፈጸመ … (ሉቃስ 4፥18-21)***

> **“ዛሬ ይህ መጽሐፍ በጆሮአችሁ ተፈፀመ ” ሲል፣ ኢየሱስ ያለው በብሉይ ኪዳን ተነግሮና ይሆናል ተብሎ የነበረው አንድ ነገር ዛሬ እውን ሆነ ነው፡፡ ይህም ኢዮቤልዩ ብለን የምንጠራውን ሃሳብ ጠቅልሎ የሚይዝ ሲሆን፣ በ49ነኛው ወይም በ50ኛው ዓመት፣ እንደ ስሌት አሠራራችሁ ማለቴ ነው፣ የብሉይ ኪዳኗ እስራኤል ሰዎችን ከዕዳ ነጻ በማውጣት ወደ ቀደሙት አባቶቻቸው ርስት፣ ወደ ነገዶቻቸው ድርሻ የምትመልስበት፣ ማለትም ቤተሰቦቻቸው በሙሴና በኢያሱ ዘመን ተሰጥቷቸው ወደ ነበረው ርስት የምትመልስበት ነው፡፡ ዘፀአትን እንደ ትልቅ፣ የብሉይ ኪዳን የመቤዠት ሁነት ካሰብነው፣ ኢዮቤልዩንም እንደ እግዚአብሔር የተሃድሶ ወሳኝ ስጦታ ልንገነዘበው ይገባል፡፡ ምክንያቱም፣ በወደቀ ዓለም ውስጥ እስከኖርን ድረስ፣ የሚያድነን መቤዠት ነው፣ ተሃድሶ ደግሞ የእግዚአብሔር ቤዝዎት አካል ነው፡፡ እናም ኢየሱስ የዚህን የኢዮቤልዩ ምልክቶች እያሳየ ይመስላል፡፡ ሰዎችን ከኢ‍ኃንንት ጭቆና፣ ከማኅበራዊ ንቀት ወይም ከማኅበረሰብ መገለል ነፃ እያወጣ ወደ ፈጣሪያቸውና ወደ አባታቸው ይመልሳቸው ነበር፡፡ (ቄስ ሚካኤል ግሎዶ)**

የምትመጣዋ የእግዚአብሔር መንግሥት ለእግዚአብሔር ታማኝ ህዝብ ድነትን እንደምታስገኝ ኢሳያስ ተንብዮ ነበር፡፡ ኢየሱስ ደግሞ ያ ቀን መድረሱን አወጀ፡፡ ይህ ጥቅስ ሉቃስ ስለ ኢየሱስ አገልግሎት ሊገልጥ የወደደውን ሞዴል፣ ማለትም ኢየሱስ መሲህ ወይም ክርስቶስ፣ በብሉይ ኪዳን ትንቢት የተነገረለት አዳኝ ለህዝቡም ድነትን በማምጣት በምድር የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚያመጣ መሆኑን በአግባቡ የሚገልጥ ነው፡፡

የኢየሱስን የናዝሬት አገልግሎት ከኢሳያሱ ጋር ካዛመደ በኋላ፣ በሉቃስ 4፥31-7፥17 ስለ ኢየሱስ ኃይልን የተሞሉ ትምህርቶችና ተዓምራት የተለያዩ ምሌዎችን ሉቃስ ይዘግባል፡፡

## ትምህርትና ተዓምራት

በዚህ ክፍል፣ ኢየሱስ በኢሳያስ 61፥1-2 የተነገረውን ትንቢት የፈፀመ መሲህ መሆኑን ሉቃስ አሳይቷል፡፡ በሉቃስ 4፥31-36 ሰዎችን ከክፉ መንፈስ ነፃ አውጥቷል፡፡ በ4፥38-42 በርካታ ሌሎች ሰዎችን ፈውሷል፡፡ በሉቃስ 5፥1-11 ደግሞ ደቀመዛሙርቱን ጴጥሮስን፣ ያዕቆብን እና ዮሐንስን ጠራ፡፡

ተመሳሳይ የሆነውንም አካሄድ በተከታዩም ጥቅስ ውስጥ እናገኛለን፣ የለምፃሙነ መንፃት በሉቃስ 5፥12-15 እና የሽባውን መፈወስ በሉቃስ 5፥17-26፣ ተከትሎ የመጣው በማቴዎስ 5፥27-32 የተመዘገበው የደቀመዝሙሩ የሌዊ ወይም የማቴዎስ መጠራት ነው፡፡

በሚቀጥሉትም ጥቅሰፐች ተመሳሳዩን እናገኛለን፡፡ ሆኖም ሉቃስ ከፈውስ ይልቅ፣ የኢየሱስን ትምህርቶች ይዘግባል፡፡ በ5፥33-39፣ በአካል አብሯቸው የሚሆንበት ወቅት ማብቂያው መድረሱን በማስተማር ስለ ፆምና ሃሴትን ስለማድረግ አስተምሯል፡፡ በ6፥1-11 ውስጥ፣ ሰንበት ለፈውስና የሰዎችን ሕይወት ለማዳን መሆኑን ኢየሱስ አስተምሯል፡፡ በ6፥12-16 ውስጥ፣ ለእስራኤል አዲስ ሥርዓትን ለማምጣት የተሾሙትን ዐሥራሁለቱን ከበርካታ ደቀመዛሙርቱ መካከል በመምረጥ ልዩ ሐዋርያቱ ማድረጉን እናያለን፡፡

በእነዚህ ተዓምራቱና ትምህርቶቹ፣ ኢየሱስ እርሱ በኢሳያስ የተተነበየው መሲህ መሆኑን ያሳየ ሲሆን፣ ምክንያቱም በነጻነት፣ በፈውስ እና ከጭቆና በማላቀቅ የእግዚአብሔርን ሞገስ የገለጠ በመሆኑ ነው፡፡

ቀጥሎም፣ በሉቃስ 6፥17-49 ረዘም ያለውን የኢየሱስን ስብከት ሉቃስ ዘግቧል፡፡ ይህ ስብከቱ በሜዳ ላይ የሰበከው ስብከት የሚባል ሲሆን፣ በማቴዎስ ምዕራፍ 5-7 ከተቀመጠው ከተራራው ስብከቱ ጋር በርካታ ተመሳሳይ ነገሮች አሉት፡፡

> **በማቴዎስ እና በሉቃስ መካከል ካሉት ውብ ንፅፅሮች መካከል አንዱ በማቴዎስ 5-7 የተራራውን ስብከት ስናገኝ፣ በሉቃስ 6 ደግሞ የሜዳ ስብከቱን ማግኘታችን ነው፡፡ ይህም የውይይት ወይም የክርክር ማብቃያ አልሆነም፡፡ እነዚህ ነገሮች አንድና ተመሳሳይ ናቸው፣ ወይስ የተለያዩ? ሁለቱም ሊባል እንደሚገባ አስባለሁ፡፡ በመጀመሪያ፣ ኢየሱስ በዚያን ወቅት ከተናገረው ነገር ሁሉ ጥቂት ቆንጠር ተደርጎ የቀረበ መሆኑን እናውቃለን፡፡ ማለቴም፣ እስኪ ማቴዎስ 5-7 አንብቡ፣ ጮክ ብላችሁ ለማንበብ የሚፈጀው ጊዜ አርባ ደቂቃዎች ነው፡፡ ኢየሱስ ሲናገር የነበረው ለሰዓታት ነበር፣ ትምህርቶቹም እንዲህ ስብስብ ያሉ አልነበሩም፡፡ ስለዚህ አሁን እኛ እየተነጋገርን ያለነው ከጥቂቷ ጋር ነው፡፡ እና፣ እያወራን ያለነው ስለ ተመሳሳይ ቅንጣቢ ነውን? አዎን ሳይሆን አይቀርም፡፡ ሊነገር የሚገባው ሁለተኛ ነገር፣ የዚያን አካባ ምልከዓ-ምድር ስናውቅ፣ ነገሩ ያስደንቀናል፡፡**

**ከቅፍርናሆም ጀርባ ኮረብቶች አሉ፣ እናም ኮረብቶቹን ተመልከታችሁ፣ ኢየሱስ ተቀምጧል፣ ሰዎችም በኮረብታው ላይ አሉ፡፡ በሌላ ጎኑ ግን፣ ጠጋ ብላችሁ ስትመለከቱት፣ ከሦት ሺህ ጫማ ከፍታ ላይ የወረደ እና ወደ ባህር ወለልነት ተለውጦ ቀስ በቀስ የረጋ የቮልካኖ ቅሪት ነው፡፡ ራቅ ብላችሁ ስትመለከቱት ደግሞ፣ እንደ ሜዳ እኔም ሆንኩ እናንተ ከበርካታ ነገሮች ጋር የምናጣቅሰው ነገር ይኖረዋል፡፡ በኮረብታ ላይ ተዳፋት ያለበት ነው፡፡ አሁን ዋናው ነገር ተገኘ፡፡ የተራራው ስብከት ስንል፣ ኢየሱስ በተራራ ላይ ተቀምጦ ነበር እና የሜዳ ስብከት ስንል፣ ነገሩ ያው ነው ጠፍጣፋ ስፍራ ነበር ማለት ነው፡፡ አስገራሚ የሆነው የመጨረሻው ነገር ይህ ነው፡፡ ሉቃስ ኢየሱስ ለሶች የሚቀረብ ሆነ የሚለውን መገረም ሊያሳየን ነው የሚፈልገው፣ ማለትም፣ ኢየሱስ በሜዳ ላይ ነበር ሲል፣ ከእኛ ጋር ሆነ ማለቱ ነው፡፡ ማቴዎስ ደግሞ እንድናይ የፈለገው ኢየሱስ ባለሥልጣን መሆኑን ሲሆን ልክ ሙሴ በሲና ተራራ እንደነበረው ማለት ነው፡፡ አሁን ለሁለቱም ምላሽ አግኝተናል፡፡ (ዶ/ር ፒተር ዎከር)**

በሜዳ ላይ ስብከቱ ውስጥ፣ ኢየሱስ አፅንዖት የሰጠበት ኢሳያስ ተንብዮ የነበረውን ተመሳሳይ ተገላቢጦሽ ነው፡፡ ድሆች ይባረካሉ፡፡ የተራቡ ይጠግባሉ፡፡ የሚያለቅሱ ይስቃሉ፡፡ ተስፋ የሌላቸውን እግዚአብሔር ይባርካቸዋል፡፡ መልካሙ የምሥራች ግን ከዚህም ርቆ ይሄዳል፡፡ ብሩካኑ እንዲከተሉትና ከዓለም እጅግ የተለዩ እንደሆኑት እንደ እግዚአብሔር መንግሥት እሴቶች እንዲኖሩ ኢየሱስ ጥሪ ያቀርብላቸዋል፡፡ ለምሳሌ፣ እንግዶችን፣ እንዲያውም ጠላቶቻቸውን እንዲወዱ ጥሪ ያቀርብላቸዋል፣ ይህም ከዓለም እሴቶች ማለትም ከእንግዶች እንድንጠነቀቅ እና ጠላቶቻችንን እንድንጠላ ከሚነግረን የሚቃረን ነው፡፡ ስለዚህም፣ የመንግሥቱ መልእክት የበረከት ብቻ ሳይሆን፣ ሥነምግባራዊ ሃላፊነትም ያለበት ነው፡፡

ከሜዳ ላይ ስብከቱ በኋላ፣ ሉቃስ ክፍሉን የሚጠቃልለው፣ ኢየሱስ ኢሳያስ የተናገረውን የፈፀመ መሆኑን በሚያስረዳ ተጨማሪ ማስረጃ ነው፡፡ ኢየሱስ የመቶ አለቃውን ልጅ መፈወሱ፣ በሉቃስ 7፥1-10 እና በሉቃስ 7፥11-16 ውስጥ፣ እንዲያውም በናይን የመበለቲቱን ልጅ ከሞት አስነሣ፡፡

ኢየሱስ በገሊላ ስለ ሰጠው አገልግሎት ሉቃስ ያቀረበው ቀጣይ ዘገባ በሉቃስ 7፥18-50 የሚገኙት በመጥምቁ ዮሐንስ ዙሪያ የሚጠነጥኑትን ታሪኮች ናቸው፡፡

## መጥምቁ ዮሐንስ

መጥምቁ ዮሐንስ ከታሰረ በኋላ፣ በእርግጥ እርሱ መሲሁ መሆኑን እንዲጠይቁለት ከደቀመዛሙርቱ ጥቂቶቹን ወደ ኢየሱስ ላከ፡፡ ኢየሱስም እርሱ ያደረጋቸውን በማሳሰብ ምላሽ ሰጠ፡፡ የኢየሱስ ተዓምራትና ስብከት በኢሳያስ 61፥1-2 የተነገረውን ትንቢት በግልፅ የፈፀመ ሲሆን፣ ኢየሱስ በእርግጥ መሲህ መሆኑንም አረጋግጠዋል፡፡ በሉቃስ 7፥22 ኢየሱስ ለዮሐንስ መልእክተኞች ምን እንደተናገረ አድምጡ

**ኢየሱስም መልሶ፡- ሄዳችሁ ያያችሁትን የሰማችሁትንም ለዮሐንስ አውሩለት፤ ዕውሮች ያያሉ፥ አንካሶችም ይሄዳሉ፥ ለምጻሞችም ይነጻሉ፥ ደንቆሮዎችም ይሰማሉ፥ ሙታንም ይነሣሉ፥ ለድሆችም ወንጌል ይሰበካል፤ (ሉቃስ 7፥22)**

ዮሐንስ ከነቢያት ሁሉ ታላቅ መሆኑን ኢየሱስ ማረጋገጡን ቀጥሏል፡፡ ሆኖም ዮሐንስ በመንግሥተ ሰማይ ከሁሉ የሚያንሰው ይበልጠዋል፡፡ ሉቃስም ይህንን ነጥብ በ7፥47-50 ኢየሱስ እግሩን ያጠበችውን ሴት ኃጢአት ይቅር እንዳለ በማብራራት ገልጦታል፡፡ ዮሐንስ እግዚአብሔር ለይቅርታ ላቀረበው ጥሪ ምልክት ይሆን ዘንድ በውሃ አጠመቀ፣ ኢየሱስ ግን ኃጢአተኞችን ይቅር በማለት፣ የታመሙትን በመፈወስ እና ለድሆች ወንጌልን በመስበክ መንግሥቱን በሰዎች የአሁን የሕይወት ልምምድ ውስጥ አመጣ፡፡

በመጥምቁ ዮሐንስ ዙሪያ ከሚያጠነጥኑ ታሪኮች በኋላ፣ በሉቃስ 8፥1-56 ውስጥ ሉቃስ ስለ ኢየሱስ ትምህርቶችና ተዓምራት የበለጠ ዘግቧል፡፡

## ትምህርቶችና ተዓምራት

በእነዚህ ተጨማሪ ትምህርቶችና ተዓምራት፣ ኢየሱስ በመንግሥቱ የምሥራች ወንጌል ላይ አትኩሯል፡፡ በሉቃስ 8፥1-15 በዘሪው ምሳሌ እና በሉቃስ 8፥16-18 በመቅረዙ መብራት ምሳሌዎች ለመንግሥቱ ወንጌል በእምነትና በመታዘዝ ምላሽ የመስጠትን ወሳኝነት ገልጧል፡፡ እነዚህኑ ተመሳሳይ ርዕሰ ሃሳቦች በሉቃስ 8፥19-21 ውስጥም የእርሱ እውነተኛ ቤተሰቦች የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰሙና የሚታዘዙ መሆናቸውን በመናገር ደግሟቸዋል፡፡

ከዚያም፣ በሉቃስ 8፥22-56 ውስጥ፣ ኢየሱስ ድነትን ወደ ምድር ያመጣ መሆኑን የሚያረጋግጡ በርካታ ተዓምራትን ሉቃስ ዘግቧል፡፡ እነርሱም፡ ኢየሱስ ማዕበሉን ፀጥ ማድረጉ፣ አጋንንትን ማስወጣቱ፣ የታመመች ሴት መፈወሱ እና የሞተችውን ልጅ ማስነሣቱ ናቸው፡፡

በመጨረሻም፣ ሉቃስ የኢየሱስን የገሊላ አገልግሎት ያጠናቀቀው፣ በሉቃስ 9፥1-50 ዐሥራ-ሁለቱን ሐዋርያት ለአገልግሎት ማዘጋጀቱን በመዘገብ ነው፡፡

## የዐሥራ-ሁለቱ ሐዋርያት ዝግጅት

በመጀመሪያ፣ በሉቃስ 9፥1-9፣ ኢየሱስ የእርሱን ዐሥራ-ሁለት ሐዋርያት እንዲፈውሱና እንዲሰብኩ ላካቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች በሉቃስ 6 ውስጥ የተለዩት ሰዎች ናቸው፡፡ ከዚያም በ9፥10-17 5000ዎችን በመመገብ ኃይሉን ገለጠ፣ ሐዋርያቱም በእርሱ ኃይልና መግቦት እንዲተማመኑ አደረገ፡፡ እነዚህ ዝግጅቶች ድምዳሜ ያገኙት በሉቃስ 9፥18-27፣ ሐዋርያቱ ኢየሱስ ለረጅም ዘመን ሲጠበቅ የነበረው መሲህ ወይም ክርስቶስ መሆኑን ሲያረጋግጡ ነው፡፡

ሉቃስ ይህንን ክፍል የሚያጠቃልለው ኢየሱስ ሐዋርያቱን ለአገልግሎት ማዘጋጀት መቀጠሉን፣ በተለይም እርሱ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ስለሚኖራቸው አገልግሎት በሚያተኩሩት ታሪኮች ነው፡፡ በሉቃስ 9፥28-36 ውስጥ ኢየሱስ በጴጥሮስ፣ በያዕቆብና በዮሐንስ ፊት መለወጡን፣ አብም ከሰማያት ራሳቸውን ለኢየሱስ እንዲሰጡ መናገሩን እናነባለን፡፡ ከዚያም ኢየሱስ በ9፥37-45 ውስጥ እጅግ ከባድ የሆነውን አጋንንት ሲያስወጣ ደግሞም በ9፥46-50 በመንግሥቱ ስለሚኖር ትልቅነት አስተማረ፡፡ በነዚህ ሁሉ ዘገባዎች፣ ደቀመዛሙርቱ የእርሱን ኃይል እንዲያውቁ፣ በኃይሉ እንዲታመኑ እና በስሙም ትሑታን አገልጋዮች በመሆን እንዲያገለግሉ እና በምድር በምትሰለጥነውም መንግሥቱ ውጤታማ መሪዎች እንዲሆኑ እያዘጋጃቸው ነበር፡፡

ከገሊላው የኢየሱስ አገልግሎት በኋላ፣ ቀጣዩ የሉቃስ ወንጌል ዐቢይ ክፍል ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገውን ጉዞ ይገልጣል፡፡ ይህም ክፍል ከሉቃስ 9፥51-19፥27 ድረስ ይዘልቃል፡፡

## ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገው ጉዞ

በዚህ ክፍል ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ የጨከነ መሆኑን ሉቃስ አምስት ጊዜ ገልጦታል፡፡ እነርሱም፡- 9፥51፣ 13፥22፣ 17፥11፣ 18፥31 እና 19፥28 ናቸው፡፡ አንዱን ለምሳሌ ብናሳ፣ እስኪ ሉቃስ 18፥31-32 ያለውን አድምጡ፡-

> ***አሥራ ሁለቱንም ወደ እርሱ አቅርቦ እንዲህ አላቸው፡- እነሆ፥ ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን፥ ስለ ሰው ልጅም በነቢያት የተጻፈው ሁሉ ይፈጸማል።***
> ***ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታልና፥ ይዘብቱበትማል ያንገላቱትማል ይተፉበትማል፤ (ሉቃስ 18፥31-32)***

እግዚአብሔር ህዝቡን ለማዳን ያቀደውን ዕቅድ ለመፈፀም፣ በኢየሩሳሌም መሞት እንኳን ቢጠይቀውም ኢየሱስ የተሰጠ መሆኑን ሉቃስ እነዚህን በመሳሰሉ ምንባቦች በግልፅ ያስቀምጣል፡፡

ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገውን ጉዞ አስመልክቶ ሉቃስ የዘገበውን በአራት ዋና ክፍሎች እንከፍለዋለን፡ በመጀመሪያ፣ ኢየሱስ ስለ ደቀመዝሙርነት ባህርይ ያስተማረው ትምህርት፤ ሁለተኛ፣ በኢየሱስና በተቃዋሚዎቹ መካከል እየገነነ ስለመጣው ግጭት የሉቃስ ዘገባ፤ ሦስተኛ፣ ደቀመዝሙርነት ስለሚያስከፍለው ዋጋ የኢየሱስ ትምህርት እና አራተኛ፣ ሰዎችን ለማዳን እግዚአብሔር ላለው እቅድ የኢየሱስ መሰጠት፡፡ አስቀድመን በሉቃስ 9፥51-11፥13 በተመዘገበው በደቀመዝሙርነት ተፈጥሮ እንጀምር፡፡

### የደቀመዝሙርነት ተፈጥሮ

ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመገንባትና ሰዎችን ለማዳን ያለው መሰጠት ለሎሌያዊ አመራር ሊያዘጋጅና ሊያሰለጥን ዐሥራ-ሁለት ሐዋርያትን እንዲመርጥ አድርጎታል፡፡ በሉቃስ 9፥51-10፥24 ውስጥ፣ ወንጌልን እንዴት እንደሚሰብኩ እና ያም ሕይወት ለእነርሱ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሚሆን አስተምሯቸዋል፡፡ ሆኖም በመንፈስ ቅዱስ እንደሚያስታጥቃቸውም ነግሯቸዋል፡፡ ከዚህ ዝግጅት በኋላ፣ እርሱ ወዳቀደለዘቸው ከተማ በመሄድ ወንጌልን እንዲሰብኩ ላካቸው፡፡

ይህንንም ተከትሎ፣ በሉቃስ 10፥25-11፥13 ውስጥ፣ ኢየሱስ ከደቀመዝሙርነት ጋር የተያያዙ ርዕሶችን፤ ለባንጀራ ሊኖር ስለሚገባ ፍቅር፣ ለእግዚአብሔር ሊኖር ስለሚገባ ፍቅር እና ስለ ጸሎት በማስተማር ሰፋ ያለ ንፅረተ-ዓለም እንዲኖራቸው አደረገ፡፡

ኢየሱስ በሉቃስ 10፥27 ስለ ፍቅር ያስተማረውን ትምህርት እንዲህ ጠቅለል በማድረግ ጀምሮታል፡

***ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም ኃይልህም በፍጹም አሳብህም ውደድ፥ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም ኃይልህም በፍጹም አሳብህም ውደድ፥ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ (ሉቃስ 10፥27)***

በዚህ ስፍራ፣ ኢየሱስ ከዘዳግም 6፥5 እና ከዘሌዋውያን 19፥18 በመጥቀስ የብሉይ ኪዳን ህግ የሚስተምረው እግዚአብሔርንና ባልንጀሮቻችንን እንዴት ልንወድድ እንደሚገባ መሆኑን አብራርቷል፡፡

ቀጣዮቹ ሁለት አንቀፆች የፍቅርን ህግ ሁለት ክፍሎች የሚገልፁ ናቸው፡፡ የ"ደጉ ሳምራዊ" ምሳሌ በሉቃስ 10፥29-37 ባልንጀራን እንዴት መውደድ እንዳለብን ያብራራል፡፡ ይህ ክፍል ጉዳት የደረሰበትን እስራኤላዊ፣ ምንም እንኳን በሁለቱ ወገኖች መካከል ውጥረት ቢኖርም ሳምራዊው ሰው እንዴት የባልንጀራ ፍቅር እንዳሳየው የሚገልፅ ታዋቂ ታሪክ ነው፡፡ ቀጥሎም፣ በሉቃስ 10፥38-42፣ እግዚአብሔርን እንዴት ልንወድድ እንደሚገባ ኢየሱስ ከማርያም ጋር ያደረገው ንግግር ምሳሌ ይሆነናል፡፡ እግዚአብሔርን ራሱን የመጀመሪያ ቅድሚያችን በማድረግ እና እርሱንም በመታዘዝ ልብ በመስማት እግዚአብሔርን መውደድ እንዳለብን ማርያም አሳይታለች፡፡

በመጨረሻም፣ በሉቃስ 11፥1-13 ውስጥ ስለ ጸሎት ባስተማረው ትምህርት ኢየሱስ ለሐዋርያት ሲሰጥ የቆየውን መመሪያ አጠናቅቆአል፡፡ በዚያም በእውነትና በፅናት ሊጸልዩ እንደሚገባ በማስተማር የእግዚአብሔርን መንግሥት በረከት የሚቀበሉት በዚያ መሆኑን አሳይቷል፡፡

**ጸሎት ለክርስቲያኖች እጅግ ወሳኝ ነው፡፡ በኢየሱስም ሕይወት ወሳኝ ክፍል ነበር፣ ወሳኝነቱንም በሕይወቱ ምሳሌነት እንመለከታለን፡፡ *ሥራዎቹ እያደጉ በሄዱ መጠን፣* አብዝቶ ይጸልያል፣ አረፍ ሲልም የእግዚአብሔርን ማበርታት ይፈልግ ነበር፡፡ በመንፈሳዊ ረገድ ራሱን ለማደስ በዘላቂነት ከአብ ጋር ግንኙነት ማድረግ እንደሚያስፈልገው ተረድቶ ነበር፡፡ *0ሥራ-ሁለቱን* ደቀመዛሙርቱን ከመምረጡ በፊት ሌሊቱን ሙሉ ጸልዮአል፣ ከእነርሱ አንዱ አሳልፎ እንደሚሰጠውም ያውቅ ነበር፡፡ እንዲያውም፣ ደቀመዛሙርቱን ሲመርጥ አስቀድሞ ወደ መስቀሉ እየተመለከተ ነበር፡፡ እንግዲህ ይህንን የመሰለ አገልግሎት ከመስጠቱ አስቀድሞ ሌሊቱን በጸሎት ማሳለፉ ከምክንያቶቹ አንዱ ነው፡፡ የኢየሱስ የጸሎት ሕይወት ለእኛ ምሳሌ ነው፡፡ በኋላም፣ ደቀመዛሙርት ስሰጡት አስደናቂ አገልግሎት ደስ እያላቸው ሲመለሱም፣ ኢየሱስ "የሰማይና የምድር ጌታ አባት ሆይ፥ ይህን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕፃናት ስለ ገለጥህላቸው አመሰግናለሁ፤" በማለት አብን አመሰገነ፡፡ እርሱ አብን ካመሰገነ፣ እኛም ልናመሰግን ይገባናል፡፡ ኢየሱስ መጸለይና ማመስገን ካስፈለገው፣ እኛም ይበልጥ ማድረግ ያስፈልገናል፡፡ ከመያዙ አስቀድሞ፣ በጌተሰማኒ ብርቱ ጸሎት ጸልዮአል፣ በመጨረሻም "አባት ሆይ፣ ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ " እያለ ይጸልይ ነበር፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ ራሱን ለአብ ያስገዛ ነበር፡፡ ኢየሱስ ከአብ ጋር ካለው ግንኙነት የተነሳ ጸለየ፣ ለሰው ዘርም ያለውን**

የማዳን ዕቅደ ለመፈፀምም ፈለገ፡፡ እኛም እንደ እግዚአብሔር ልጆች፣ ጸሎታችንና ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛታችን ለሕይወታችን ወሳኝ መሆኑን የእርሱ ምሳሌነት ያስተምረናል፡፡ (ዶ/ር ፒተር ቾው፣ ትርጉም)

ክርስቲያኖች ሊጸልዩ የሚያስፈልግበት ዋናው ምክንያት በጸለይን ቁጥር፣ በክርስቶስ ያለንን እምነት መግለጣችን ሲሆን፣ በወንጌልም ማረፋችንን የሚሳይ ነው እላለሁ፡፡ የምንጸልይበት ብቸኛ ምክንያት ኢየሱስ ለኃጢአታችን በመሞቱ ነው፤ ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን መቅረብ የምንችልበትን ዕድል ሰጠን፡፡ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነትና በድፍረት በጸሎት እንቀርባለን ምክንያቱም ኢየሱስ መንገዱን ከፍቶታልና ነው፡፡ እናም፣ የምንጸልይበት የመጀመሪያ ምክንያት የወንጌል ልምምድ ስለሆነ ነው፡፡ የምንጸልይበት ሁለተኛው ምክንያት በሁሉም ነገር በእግዚአብሔር በዘላቂነት የመታመናችን ምልክት ስለሆነ ነው፡፡ ወደ እርሱም እንደ አባት፣ ልጆቹን እንደሚወድድና እንደሚባርክ በማመን የእለት እንጀራችንን እንዲሰጠን ለመለመን እንቀርባለን፡፡ በሌላም መንገድ እግዚአብሔርን የምናመልክበትም መንገድ ሲሆን፣ የሚገባው መሆኑን እናውጃለን፣ እናደንቀዋለን ደግሞም ከእርሱ ጋር ግንኙነት እናደርጋለን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው፣ በማያቋርጥ ጸሎት ውስጥ ስንሆን፣ ማለትም በየዕለቱ በእግዚአብሔር ህላዌ ውስጥ ስንራመድ፣ እግዚአብሔር እርሱ በሕይወታችን ውስጥ ያሉትን ሸክሞች ሁሉ የሚሸከምልን አምላክ መሆኑን እንገነዘባለን፣ በጸሎት ውስጥ ይህ እውነታ አለ፡፡ (ዶ/ር ኬ. ኤሪክ ቶኔስ)

ጆን ዌስሊ ጸሎትን ወደ እግዚአብሔር የመቅረቢያ ዐቢይ መንገድ ደግሞም ጸጋን የመቀበያ ላዕላይ መንገድ ነው ይለዋል፡፡ በመሠረቱ፣ የክርስትናን ታሪክ በምትመለከቱበት ወቅት፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብና ጸሎት ተቀዳሚ መንፈሳዊ ልምምዶች ናቸው፡፡ እኔ እንደማስበው ጸሎት በጣም አስፈላጊ የሚሆነው ክርስትና ሊያራምደው የሚፈልገውን ዓይነት ግንኙነት ከእግዚአብሔር ጋር እንዲኖረን ስለሚያደርግ ነው፡፡ ስንጸልይ፣ ከእግዚአብሔር ጋር እንነጋገራለን፣ እግዚአብሔር ለእኛ የሚናገረውን እናደምጣለን እናም ለሰማነው ነገር መልስን እንሰጣለን፡፡ ያም የግንኙነቱ መሠረት ነው፡፡ እግዚአብሔርም በእርግጥ ለእኛ የሚፈልገው፣ ከእርሱ ጋር ግንኙነት እንዲኖረን ነው፡፡ ወደ ኋላ መለስ ብላችሁ ስትመለከቱ እግዚአብሔር ከአዳምና ከሔዋን ጋር ግንኙነት እንዲኖረው ፈልጎ በገነት ውስጥ ይመላለስ ነበር፡፡ ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር የምንነጋገርበትና የምንመላለስበት መንገድ ነው፡፡ አንድ ጥንታዊ መዝሙር "እርሱ ከእኔ ጋር ይነጋገራል ይነጋገራልም የእርሱም እንደሆንሁ ይነግረኛል" ይላል፡፡ ማለቴም፣ በምትጸልዩበት ወቅት የክርስትናን ልብ ታገኙታላችሁ፣ ምክንያቱም ጸሎት ተዘምዶአዊ ነው፡፡ (ዶ/ር ስቲቭ ሃርፐር)

በደቀመዝሙርነት ተፈጥሮ ላይ ኢየሱስ ካስተማረው ትምህርት በኋላ፣ በኢየሱስና በአይሁድ መሪዎች መካከል እየጨመረ ስለመጣው ግጭት ሉቃስ በ11፥4-15፥32 ውስጥ አትኩሮት ያደርጋል፡፡

## እያደገ የመጣው ግጭት

በዚህኛው ጉዞው፣ ኢየሱስ ቢያንስ በሦስት ምክንያቶች ሆን ብሎ የአይሁድን መሪዎች ተቃውሟል፡፡ በመጀመሪያ፣ ለእግዚአብሔር ህዝብ እየሰጡ ስላሉት ደካማ አመራር ሊነቅፋቸው ፈልጓል፡፡ ሁለተኛ፣ ሰዎችን ወደ ራሱ መንግሥት ሊጠራ ፈልጓል፡፡ ሦስተኛ፣ በኢየሩሳሌም እንዲሰቅሉት፣ በዚያም የህዝብን ሁሉ ኃጢአት ለማስወገድ ማስተሰረያን ሊያቀርብና በእነርሱም ላይ ንጉሥ ሆኖ ብድራቱን ሊቀበል ፈልጓል፡፡

ለምሳሌ፣ በሉቃስ 11፥14-28፣ አይሁድ ኢየሱስን "የአጋንንት አለቃ" ብለውታል፡፡ ኢየሱስም ከቁጥር 29-53 ውስጥ ስለ ክፋታቸው በመገሰፅ ምላሽ የሰጣቸው ሲሆን ወዮታንም አውጇባቸዋል፡፡

በሉቃስ 12፥1-3፣ እንደ ፈሪሳውያን ግብዞች እንዳይሆኑ ኢየሱስ ህዝቡን አስጠንቅቋል፡፡ ከቁጥር 4-21፣ የአይሁድን ምኩራቦች፣ ገዢዎችና ባለሥልጣናት ልምምዶች በትር ሰንዝሮባቸዋል፡፡ ከቁጥር 22-32፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለሚሹ የሚያስፈልጋቸውነ ሁሉ እንደሚያሟላላቸው አፅንዖት በመስጠት፣ እንደ አይሁድ መሪዎች ዓለማዊ ነገሮችን እንዳያሳድዱ ነግሯቸዋል፡፡ ከቁጥር 33-59 ደግሞ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ከማያስቀድሙ ጋር የእርሱ ተከታዮች መጋጨታቸው አይቀሬ መሆኑን ኢየሱስ አስጠንቅቋቸዋል፡፡

በሉቃስ 13፥1-9 ውስጥ፣ እስራኤል በጠቅላላ በኃጢአቱ ንስሓ እንዲገባ ጥሪን በማቅረብ ኢየሱስ የአይሁድን መሪዎች መቃወሙን ቀጥሏል፡፡ ከዚያም ከቁጥር 10-17 ውስጥ፣ በሰንበት ቀን ሽባውን በመፈወስ ግጭቱን አባብሶታል፣ ይህም የምኩራቡን አለቆች እጅግ አስቆጥቷል፡፡ ከቁጥር 18-30 ውስጥ፣ ግንባር ቀደም የሆኑ የአይሁድ መሪዎችንና ተከታዮቻቸውን በግልፅ በመውቀስ እንገባለን ያሉ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንደማይገቡ ኢየሱስ አስተምሯል፡፡ በመጨረሻም፣ ከቁጥር 31-35 ውስጥ፣ ሊገድለው ባቀደው የአሕሁድ ንጉሥ ሄሮድስ፣ እና በኢየሱስ መካከል ግጭቱ እየከረረ መምጣቱን ሉቃስ ዘግቧል፡፡

በሉቃስ 14 ውስጥ፣ ኢየሱስ የአይሁድን መሪዎች ይበልጥ አስቆጣቸው፡፡ ከቁጥር 1-24፣ በሰንበት ቀን አንድን ሰው ፈወሰ እና የአይሁድን መሪዎች ዓለማዊ እሴቶች ነቀፈ፡፡ አንዳቸውም እንኳን የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደማይወርሱ ተናገረ፡፡ ከዚያም ከቁጥር 25-34፣ እርሱን ከሚቃወሙ ሰዎች ጋር ከሚገጥማቸው ነገር የተነሳ ተከታዮቹ በዚህ ያላቸውን ነገር ሁሉ ሊያጡ እንደሚችሉ ተከታዮቹን አስጠንቅቋል፡፡

ኢየሱስ በ15፥1-2 መግቢያ ከሰጠ በኋላ፣ ስለጠፉ ነገሮች በተናገረው ምሳሌ ከአይሁድ መሪዎች ጋር የነበረውን ጠብ ይቀጥለዋል፡፡ የጠፋው በግ፣ የጠፋው ሳንቲም እና የጠፋው ልጅ፡፡ በእያንዳንዱ ታሪክ ውስጥ የእርሱ ህዝብ የአይሁድን የህግ መምህራንና የፈሪሳውያንን ግብዝነት እንዲንቁ እና በዓለም ላይ ከሚገኙ የጠፉ ኃጢአተኞች መካከል ልጆቹን ሲያገኝ ደስ እንዲላቸው ኢየሱስ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

በደቀመዝሙርነት ተፈጥሮ ላይ የኢየሱስን ትምህርት እና ከአይሁድ መሪዎች ጋር እየተፋፋመ የመጣውን ግጭት ከዘገበ በኋላ፣ በሉቃስ 16፥1-18፥30 ውስጥ ደቀ መዝሙርነት ስለሚያስከፍለው ዋጋ በተናገረበት የኢየሩሳሌም ጉዞው ላይ ሉቃስ ትኩረቱን ያደርጋል፡፡

## ደቀመዝሙርነት የሚያስከፍለው ዋጋ

በእርሱ መንግሥት ውስጥ የሚኖራቸው ሕይወት በእርሱ ሕይወት የተቃኘ ሊሆን እንደሚገባው ተከታዮቹ ይረዱ ዘንድ ኢየሱስ ይፈልጋል፡፡ በዓለማዊ መሪዎች ይሰደዳሉ ደግሞም ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነው የመዝለቅ ትግል ይኖርባቸዋል፡፡ ከ16፥1-17፥10 ጀምሮ፣ ደቀመዝሙርነት ያለንን ነገር ሁሉ እንደ እግዚአብሔር ንብረት ማየትን እንደሚያካትት ኢየሱስ አስተምሯል፡፡ በተጨማሪም ምድራዊ በረከቶች እንቅፋት እንደሚሆኑ እንዲያውም ባለጠጎች እውነተኛውን ወንጌል እንዳያውቁና እንዳይቀበሉ እንደሚያደርጋቸው አስጠንቅቋል፡፡ በመጨረሻም፣ እምነትንና ንስሓን ያበረታታ ሲሆን፣ የቱንም ያህል መልካም ብናደርግ፣ እኛ በጣም ጥሩ ያልነው እግዚአብሔር ከሚጠብቅብን በላይ እንደማይሆን አስረግጦ ተናግሯል፡፡

በ17፥11-18፥8 ውስጥ፣ በዚህ ዓለም ላይ በሚመጣው የመጨረሻ ፍርድ ላይ ኢየሱስ አተኩሯል፡፡ በዚህ ሕይወታችን የምናገኛቸው መልካም ነገሮች፤ ማለትም፣ ጤና፣ ሀብት እና ፍትህ የእግዚእብሔርን መልካምነት እንድናይ ሊያደርጉን የሚገባ ሲሆን እግዚአብሔር በእነርሱ እንዲባርከን ልንጸልይ ይገባናል፡፡ ግን በመጨረሻው ፍርድ ወቅት ሁሉም ሊጠፉ ተመድበዋል፡፡ እውነተኛ ብልጥግና፣ ጤና እና ፍትህ የሚመጣው የእግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥት ብድራት ሆኖ ብቻ ነው፣ ስለዚህም የእኛ ተስፋ ሊኖር የሚገባው በዚያ ነው፡፡

ከእነዚህ ሃሳቦች በተጓዳኝ፣ በሉቃስ 18፥9-30 ውስጥ በትኅትና ላይ በማትኮር ኢየሱስ ይህንን ክፍል ያጠቃልለዋል፡፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ይቅርታ፣ በረከትና የዘላለምን ሕይወት የሚወርሱት ትሁታን ብቻ ናቸው፡፡

ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገውን ጉዞ ሉቃስ ያጠቃለለው ሰዎችን ለማዳን እግዚአብሔር ያቀደውን ዕቅድ ለማስፈጸም የነበረውን መሰጠት በ18፥31-19፥27 በመግለፅ ነው፡፡

## የኢየሱስ መሰጠት

ኢየሱስ ለእግዚአብሔር ዕቅድ ያለውን መሰጠት ያሳየበት የመጀመሪያ መንገድ በሉቃስ 18፥31-34 ስለራሱ ሞት አስቀድሞ በመናገር ነው፡፡ ሰዎችን ለማዳን ሊሞት እንደሚገባው ኢየሱስ ያውቅ ነበር እናም የአባቱን ዕቅድ ለመከተል ቆርጦ ነበር፡፡

ይህንንም ተከትሎ፣ ሊያድናቸው የመጣላቸውን ሰዎች በመባረክ ማለትም፣ በሉቃስ 18፥35-43 ዐይን-ስውሩን በመፈወስ፣ በሉቃስ 19፥1-10 ቀራጩን ዘኬዎስን በመጥራት ለእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ያለውን መሰጠት ኢየሱስ አሳይቷል፡፡ እነዚህ ሰዎች ከማኅበረሰቡ የተገለሉ ሰዎች ነበሩ፡፡

ሆኖም ከኢሳያስ 61፥1-2 ከተሰጠው ተስፋ ጋር በሚጣጣም መንገድ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ታላቅ በጎነት ይቀበሉ ጀመር፡፡ በሉቃስ 19፥9-10 ኢየሱስ ስለ ዘኬዎስ እንዲህ ተናግሯል፡

*… እርሱ ደግሞ የአብርሃም ልጅ ነውና ዛሬ ለዚህ ቤት መዳን ሆኖለታል፤ የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአለና አለው። (ሉቃ 19፥9-10)*

በመጨረሻ፣ በሉቃስ 19፥11-27 ውስጥ፣ ኢየሱስ ለአገልጋዮቹ ገንዘቡን ሰጥቶ ወደ ሩቅ አገር ስለሄደ ንጉሥ የሚተርከውን ምሳሌ ይናገራል፡፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ውርስን ማግኘት የምንፈልግ ከሆነ፣ ኢየሱስ እንዳደረገው ለእግዚአብሔር እቅድ የተሰጠን ልንሆን ይገባናል፡፡

ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገውን ጉዞ ከገለጠ በኋላ፣ በኢየሩሳሌም የሰጠውን አገልግሎት ሉቃስ ዘግቧል፡፡ ይህም የሉቃስ ወንጌል አምስተኛ ክፍል ሲሆን ከ19፥28-21፥38 ይዘልቃል፡፡

## በኢየሩሳሌምና በአቅራቢያዋ የኢየሱስ አገልግሎት

ኢየሱስ በኢየሩሳሌም በሰጠው አገልግሎት ላይ ሉቃስ የሚያቀርበው ዘገባ የሚጀምረው በሉቃስ 1928-44 ሲሆን፣ በዚያም ሰዎች ኢየሱስን በሆታና በምስጋና ተቀብለውት ወደ ኢየሩሳሌም ገብቷል፡፡

ወደ ከተማ መግባቱን ተከትሎ፣ ኢየሱስ ያደረገው የመጀመሪያ ነገር ነጋዴዎችን በማባረር ቤተመቅደሱን ማንፃት ነው፡፡ ይህ ክስተት የሚገኘው በሉቃስ 19፥45-46 ውስጥ ነው፡፡ ይህ ማንፃት የአይሁድን ሕይወትና አምልኮ ያረከሰውን ልምምድ የኮነነ ነበር፣ በዚህም የአይሁድን መሪዎች ዘልፏል፡፡

**ልክ በርካታ የአዲስ ኪዳን ምንባቦችን ለመረዳት እንደምናደርገው ሁሉ፣ የኢየሱስን መቅደስን የማንፃት ተግባር ለመረዳትም የብሉይ ኪዳኑን ታሪካዊ ዳራ ማግኘት አለብን፡፡ ወደ ብሉይ ኪዳን ተመልሰን ማጣቀስ ይገባናል፡፡ 1ኛ ነገሥት መጽሐፍ፣ ምእራፍ 8፣ የመቅደሱን መመረቅ ይዘግብልናል፡፡ መቅደሱ ለረጅም ዓመታት በመገንባት ላይ ነበር፡፡ ሲጠናቀቅ፣ ንጉሥ ሰሎሞን እና እስራኤላውያን መቅደሱን ለመመረቅ ተሰበሰቡ፡፡ ንጉሥ ሰሎሞንም፣ "ባሪያህና ሕዝብህ እስራኤል ወደዚህ ስፍራ የሚጸልዩትን ልመና ስማ በማደሪያህ በሰማይ ስማ ሰምተህም ይቅር በል።" በማለት ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፡፡ በተጨማሪም፣ ንጉሥ ሰሎሞን ስለ እግዚአብሔር ታላቅ ስም የሰሙ መጻተኞች፣ ከሩቅ አገር ቢመጡና ወደ መቅደሱ አቅንተው ቢለምኑ፣ እግዚአብሔር ጸሎታቸውን እንዲሰማ በዚያም በምድር ያሉ ህዝቦች ሁሉ የእግዚአብሔርን ስም እንዲያውቁና እንዲፈሩት፣ መቅደሱም የተገባው ስለ ስሙ እንደሆነ እንዲያውቁ ጸልዮአል፡፡ ስለዚህም፣ በኢየሱስ ዘመን፣ የሃይማኖቱ መሪዎች መቅደሱን የወንበዴዎች ዋሻ ሲያደርጉት፣ ድርጊቱ ለስሙ ስድብ ይሆናል፣ ምክንያቱም መቅደሱ ከስሙ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር፣**

***ኢየሱስ መቅደሱን ሲያነፃ፣ ተምሳሊታዊ ፍቺ አለው፡፡ መቅደሱ ወደ ኢየሱስ ወደራሱ ያመለክታል ምክንያቱም እርሱ እውነተኛውና የመጨረሻው መቅደስ ነውና፡፡ በኢየሱስ ስም አማካይነት ወደ አብ እስከጸለይን ድረስ፣ ኢየሱስ አህዛብ ሁሉ ለጸሎት ወደ እርሱ የሚቀርቡበት የመቅደሱ የዚህ ዘመን እውነታ ነው፡፡ ስለዚህ፣ መቅደሱን ከብሉይ ኪዳን አንፃር ከተረዳነው፣ ኢየሱስ መቅደሱን የማንፃቱን ወሳኝነት እና ከምትመጣዋ የእግዚአብሔር መንግሥት ጋር ያለውን ግንኙነት እናያለን፡፡*** (ዶ/ር ፒተር ቾው፣ ትርጉም)

***ኢየሱስን በጣም ያስቆጣው ነገር ተግባሩ የተፈፀመበት ክልል የአህዛብ አደባባይ መሆኑ ሲሆን፣ በዚያም ህዝቦች ሁሉ በመምጣት፣ የፍጥረተ-ዓለሙ ፈጣሪወደሆነው ፈጣሪ መቅረብ የሚችሉበት ስፍራ ነበር፡፡ ለአይሁድ ብቻ ወደተፈቀደው፣ ወደ ውስጠኛው አደባባይ ሊገቡ አይችሉም፣ የውጪው አደባባይ ግን ለህዝቦች ሁሉ፣ ለአህዛብ ነበር፡፡ ወደዚያ መምጣትም መጸለይም ይችሉ ነበር፡፡ ከዚህም የምናየው ነገር የሚጸልዩበትን ስፍራ አሳጥተዋቸው የነበረ መሆኑን ነው፡፡ የዚያ ስፍራ እውነተኛ ዓላማ የነበረው ነገር ተለውጦ አህዛብ ስፍራ አጥተው ነበር፡፡ ኢየሱስም ያደረገው መቅደሱን ወደ ዓላማው መመለስ መሆኑን እናያለን፡፡ ያም ማለት ያንን ስፍራ በማንፃት አህዛብ ለጸሎት እንዲመጡበት በማድረግ ስፍራውን ማደስ ነው፡፡*** (ዶ/ር ግሬግ ፔሪ)

በሉቃስ 19፥47-21፥38 ውስጥ እንደምናነብበው፣ ኢየሱስ ቀጣዮቹን ቀናት ያሳለፈው ስለ እግዚአብሄር መንግሥት በመናገር፣ በመቅደሱ አደባባዮች በማስተማር ነበር፡፡ በዚህ ወቅት፣ እርሱ ልምምዳቸውን ሲኮንን እነርሱ ደግሞ የእርሱን ሥልጣን ሲገዳደሩ ከአይሁድ መሪዎች ጋር የነበረው ግጭት ተፋፍሞ ነበር፡፡ በሉቃስ 20፥20 ሊቀ ካህናቱና የህጉ መምህራን ያደረጉትን አድምጡ፡

***ሲጠባበቁም ወደ ገዢ ግዛትና ሥልጣን አሳልፈው እንዲሰጡት ጻድቃን መስለው በቃሉ የሚያጠምዱትን ሸማቂዎች ሰደዱበት። (ሉቃስ 20፥20)***

ከፉ ሰዎች ሊያጠምዱት ስለሞከሩ ብቻ ኢየሱስ ስብከቱን አላቆመም፡፡ ይልቁኑ፣ በአደባባይ ገሰፃቸው፡፡ በሉቃስ 20፥46-47 ለመንጋው እንዲህ ተናግሯል፡

***ረጃጅም ልብስ ለብሰው መዞር ከሚፈልጉ፥ በገበያም ሰላምታ፥ በምኵራብም የከበሬታ ወንበር፥ በምሳም የከበሬታ ስፍራ ከሚወዱ ከጻፎች ተጠበቁ፤ የመበለቶችን ቤት የሚበሉ ጸሎታቸውንም በማስረዘም የሚያመካኙ፥ እነዚህ የባሰ ፍርድ ይቀበላሉ አለ።***

ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲቃረብ፣ እርሱን እንደሚያድናቸው መሲህ ሊቀበሉ አለመፍቀዳቸው፣ የከተማዪቱን ውድቀት ወደመተንበይ መርቶታል፡፡ ሆኖም ይህ አሰቃቂ ውድቀት የታላቁ ፍርድ ቅምሻ ብቻ ነው፡፡ በመጨረሻው ቀን፣ ኢየሱስ በክብር ሲመለስ፣ እያንዳንዱ ሰው በፊቱ መልስን ይሰጣል፡፡ በዚህም ምክንያት፣ በየዘመናቱ የሚገኙ ደቀመዛሙርቱ እርሱን በትጋት እንዲታዘዙና መመለሱንም በጥንቃቄ እንዲጠብቁ ኢየሱስ ጥሪ ያቀርባል፡፡

በኢየሩሳሌም የኢየሱስ አገልግሎት ከተዘገበ በኋላ፣ የሉቃስን ወንጌል የመጨረሻ ዐቢይ ክፍል እናገኛለን፡፡ ያም፣ በሉቃስ 22፥1-24፥53 ውስጥ የሚገኘው ከኢየሩሳሌም ውጪ ኢየሱስ የመሰቀሉና የትንሣኤው ትረካ ነው፡፡

# የኢየሱስ ስቅለትና ትንሣኤ

በወንጌሉ በዚህኛው ክፍል ውስጥ፣ ኢየሱስ እንዴት ለህዝቡ ድነትን እንዴት እንዳመጣ ሉቃስ ያብራራል፡፡ ራሱን የስርየት መስዋእት አድርጎ በማቅረብ የሰማያዊ አባቱን ፈቃድ ፈጽሟል፡፡ እናም የአባቱ የዳዊት ዙፋን ተሰጥቶታል ስለዚህም እርሱ አሁን ህዝቡን ንጉሣቸው ሆኖ ይገዛቸዋል፡፡

ስለ ኢየሱስ ስቅለትና ትንሣኤ ሉቃስ ያቀረበው ዘገባ በሁለት ክፍሎች ይከፈላል፡ የኢየሱስ መያዝ ፣ለፍርድ መቅረብ እና ሞቱ ትንሣኤውና ዕርገቱ፡፡ አስቀድመን በሉቃስ 22፥1-23፥56የኢየሱስን መያዝ፣ ለፍርድ መቅረብና ሞት እንመልከት፡፡

## መያዝ፣ ለፍርድ መቅረብና ሞት

የኢየሱስ መያዝ፣ ለፍርድ መቅረብና የሞት ዘገባ የሚጀምረው በሉቃስ 22፥1-6 ውስጥ ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት በተደረገ ሴራ ነው፡፡ ከዚያም፣ ከቁጥር 7-38 በሚገኘው የመጨረሻ ራት ወቅት፣ ይሁዳ አሳልፎ እንደሚሰጠው፣ ጴጥሮስም ኢየሱስን አልተከተልኩም ብሎ እንደሚክደው ኢየሱስ አስቀድሞ ተናገረ፡፡ በእነዚህ ጭልም ባሉ ትንቢቶች መካከል ግን በመንግሥቱ ውስጥ ደቀመዛሙርቱ ስለሚኖራቸው ስፍራ እና እነዚህን ሁሉ ክስተቶች እንደሚቆጣጠር ተናገረ፡፡

ከጌታ ራት ቀጥሎ፣ በሉቃስ 22፥39-46 ውስጥ፣ በቀራኒዮ ኮረብታ ኢየሱስ የጸለየውን ጸሎት እናገኛለን፡፡ በዚህ ጸሎት ኢየሱስ በብርቱ ምጥ ውስጥ ነበር፣ እንደ ደም ያለ ላብም ያልበው ነበር እናም የሚቻል ቢሆን አብ በአንድ መንገድ መሰቀሉን ቢያስቀርለትፈልጎ ነበር፡፡ በዚህ ሁሉ ግን፣ ኢየሱስ በአብ ላይ የነበረው ጽኑ መታመን ወይም ለአብ ዕቅድ ያለው መሰጠት አልተናወጠም፡፡

በሉቃስ 22፥47-53 የተመዘገበው የኢየሱስ መያዝ በቁጥር 54-62 የጴጥሮስ ክህደት የተመዘገበበትን ትዕይንት፣ በአይሁድ መሪዎች፣ በጲላጦስና በሄሮድስ ፊት የኢየሱስን ለፍርድ መቅረብ ደግሞ በ22፥63-23፥25 አስከትሎ መጣ፡፡ ሄሮድስና ጲላጦስ ሁለቱም ኢየሱስን ለሞት የሚያበቃው ጥፋት በሮም ላይ እንዳልፈፀመ አረጋግጠዋል፡፡ ሆኖም ፣ ጲላጦስ በአይሁድ መሪዎችና በህዝቡ ግፊት ንፁሁን ኢየሱስ እንዲሰቀል ፈረደበት፡፡

> **በኢየሱስ ለፍርድ መቅረብና መሞት ወቅት ኢየሱስ በህዝቡና በጲላጦስ ፊት ሲቆም ህዝቡ ለኢየሱስ ይሰጥ የነበረው ምላሽና ኢየሱስ እንዲገደል በርባን ግን እንዲፈታላቸው የመጠየቃቸውን ነገር ከወንጌላት ሲያነብቡ ሰዎች ግር ይላቸዋል፡፡ አንዱ ነገር የሰው ልጅ ኃጢአት ጥልቀት ምን ያህል እንደሆነ ልብ ማለት ሲሆን፣ ያም ሰዎች በጣም ኃጢአተኞች እንደሆኑ ማወቅ እና ለኢ-ፍትሃዊነት እንደምንዳረግ መረዳት ነው፡፡ ስለዚህም በህዝብ ጩኸት ልንወሰድ በዚያን ወቅትና ሁኔታም ውስጥ ታዋቂና ዝነኛ ያደርገናል ብለን ለምናስበው ነገር ስህተት መሆኑን እያወቅን እንኳን ልንሰጥ**

**እንደምንችል፣ የጠሳሰተም ነገር እንደምናደርግ እሙን ነው፡፡ እንደማስበውም በኢየሱስ ለፍርድ መቅረብ ወቅት የምናስተውለው ዐቢይ ነገር ያ ነው፡፡ በዚያን ወቅት በዚያ ስፍራ የነበሩ ሰዎች ከፈሪሳውያን ጋር የተስማሙና በኢየሱስ ላይ በአንድነት ተነስተውበት የነበሩ እንደሆኑም በልቡናችን መያዝ ሌላው ነገር ነው፡፡ ኢየሱስን ይፈሩት የነበሩት ሊቀ ካህናቱ፤ በኢየሱስ ላይ አንድ ነገር ካላደረጉ የሮም መንግሥት አንድ ነገር ያደርግብናል ብለውም ሰግተው ነበር፡፡ ስለዚህም በአንድ ጎኑ ያንን መሳይ በህዝብ የታጀበ ተግባር ሲፈፅሙ ታያላችሁ፡፡ በፈሪሳውያን ማታለል በከንቱ የሚነዳ ወኔ የሌለውን ህዝብ፣ ምንም ይሁን ምን ይህ ኢየሱስ የሚባል ይወገድልን የሚል በተሳሳተ ነገረ-መለኮት የተነዳ ህዝብ ነበር፡፡ ስለዚህ የተሰበሰበው ህዝብ ሁሉም ህዝብ ሳይሆን ኢየሱስን ይቃወም የነበረው ህዝብ እንደነበር እንረዳለን፡፡ በመጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያን ወስጥ የነበሩት የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በጠቅላላ፣ በእርግጥ አይሁድ ነበሩ፣ ሐዋርያትም አይሁዳውያን ነበሩ፣ ኢየሱስ ራሱ አይሁድ ነበር እናም ከኢየሱስ ጋር በአዎንታዊ መንገድ የሚራመዱ በርካታ አይሁድም እንደነበሩ ማስታወስ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ በመስቀል ላይ እንዲገደል ጩኸት ያሰሙት ሰዎች ኢየሱስ ሲያገለግል በነበረ ወቅት የተጋፈጣቸው ጥቂት ቡድኖች እንደሆኑ የታወቀ ነው፡፡ (ዶ/ር ፍራንክ ቴይልማን)**

ማራኪ የሆነው ነገር፣ ስለ ኢየሱስ መያዝ እና ለፍርድ መቅረብ ሉቃስ ያቀረበው ዘገባ ያተኮረው ስለሚመጣው የኢየሱስ ሞት ሳይሆን፣ በእርሱ ክርስቶሳዊ ማንነት ላይ ነው፡፡ በሉቃስ 22፥67-70 በኢየሱስና በአይሁድ መሪዎች መካከል ስለነበረው ልውውጥ እስኪ አድምጡ፡

***ክርስቶስ አንተ ነህን? ንገረን አሉት። እርሱ ግን እንዲህ አላቸው፡- ብነግራችሁ ኢታምኑም፤***
***ብጠይቅም አትመልሱልኝም አትፈቱኝምም።***
***ነገር ግን ከአሁን ጀምሮ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ኃይል ቀኝ ይቀመጣል።***
***ሁላቸውም። እንግዲያስ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህን? አሉት። እርሱም፡- እኔ እንደ ሆንሁ እናንተ ትላላችሁ አላቸው። (ሉቃስ 22፥67-70)***

በዚህ ምንባብ፣ ኢየሱስ ራሱን ከክርስቶስ፣ ከሰው ልጅ እና ከእግዚአብሔር ልጅ ጋር አንድ አድርጓል፡፡ እነዚህ ሁሉ አባባሎች እርሱ በብሉይ ኪዳነ የተተነበየለት መሲህ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡

መያዙን ተከትሎም፣ በሉቃስ 23፥26-49 ውስጥ የኢየሱስ መሰቀል ተገልጧል፡፡ በቁጥር 43 እና 46 ውስጥ፣ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሆኖ የተናገራቸውንና ሌሎቹ ወንጌላት ያላሰፈሩልንን ሉቃስ ሁለት ጊዜ ጠቅሶልናል፡፡ እነዚህ ሁለቱ ቃላት ሉቃስ በወንጌሉ ደጋግሞ ያነሳቸውን ነጥቦች፣ በመጀመሪያ፣ ኢየሱስ ተስፋ ለሌላቸው መራራቱን፤ ሁለተኛ ደግሞ፣ ኢየሱስ እነዚህን ሁሉ ሁኔታዎች ሊቆጣጠር የሚችለውን አባቱን መታመኑን ያመለክታሉ፡፡ በሉቃስ 23፥43 ውስጥ፣ በመስቀል ላይ ከጎኑ ለተሰቀለው ሰው ኢየሱስ በርኅራኄ መመለሱ፣ በእነዚህም ቃላት ማጽናናቱን እናያለን፡

***እውነት እልሃለሁ፥ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው። (ሉቃ 23፥43)***

በቁጥር 46 ደግሞ እንዲህ በማለት ወደ አባቱ ጮኸ፡

*አባት ሆይ፥ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ አለ። (ሉቃስ 23፥46)*

ጌታ ከመሞቱ በፊት የነበሩት የመጨረሻ ወቅቶች ስለ ሌሎች በመራራት እና በአባቱ ላይ ባለው መታመን የተሞሉ መሆናቸውን ሉቃስ ግልፅ ያደርጋል፡፡ ከዚያም፣ በሉቃስ 23፥50-56 ውስጥ፣ ኢየሱስ ከድንጋይ በተጠረበ መቃብር መቀበሩን እና ሰንበትም ሊገባ ከመቃረቡ የተነሳ ሰውነቱ ለቀብሩ ሊዘጋጅ አለመቻሉን ሉቃስ ዘግቦልናል፡፡

የሉቃስ በስደት ላይ ያሉ አንባቢዎች ከኢየሱስ መከራ ጋር ሊመሳሰሉ እንደሚችሉ ማየት አዳጋች አይሆንም፡፡ በየትኛውም ስደት ቢፀኑም፣ ኢየሱስ በከፋ ሁኔታም ፀንቷል፡፡ ከዚህም የሚበልቀው፣ እርሱ ያንን ያደረገው ስለ እነርሱ ነው፡፡ ጌታቸው ስለ እነርሱ ሲል መከራ ለመቀበል እና ሊሞትም ከፈቀደ፣ በእርግጠኝነት እነርሱም ስለ እርሱ መከራን ሊቀበሉና ሊሞቱለትም የገባል፡፡ ይህ ግን ባዶ ውለታ ብቻ አይደለም፡፡ ኢየሱስ ስለ መታዘዙና ስለ መከራው ብድራትን ከተቀበለ፣ የእርሱ ታዛዥ ተከታዮችም ብድራትን ይቀበላሉ፡፡

በመጨረሻ፣ የኢየሱስን መያዝ፣ ለፍርድ መቅረብና ሞት ከገለፀ በኋላ፣ ሉቃስ ወንጌሉን የደመደመው ስለ ኢየሱስ ትንሣኤና ዕርገት በሉቃስ 24፥1-53 በመዘገበ ነው፡፡

# ትንሣኤና ዕርገት

በሉቃስ 24፥1-12 ውስጥ፣ የኢየሱስ መቃብር ባዶ መሆኑን፣ የመልአክ መልእክተኛ መገለጡን እና የደቀመዛሙርቱን ግራ መጋባት የወለደው አለማመን ክስተት ሉቃስ ዘግቧል፡፡ አስቀድሞ እንደተናገረው፣ ኢየሱስ ከሞት ተነሥቷል፡፡ በእርሱና በእርሱ ባመኑት ላይ ሞት ላይሰለጥን ሞትን ድል አድርጓል፡፡

ሉቃስ 24፥13-35 በዚያው ቀን ቆየት ብሎ፣ ኢየሱስ በኤማሁስ መንገድ ላይ ከደቀመዛሙርቱ ሁለቱን የማግኘቱን ታሪክ ያነሳልናል፡፡ ስለ አገልግሎቱና ስነመነሣቱ በብሉይ ኪዳን የተጻፈውን እንዲያነቡ አስተምሯቸዋል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ የተመዘገበ ነገር ሁሉ ወደ ኢየሱስና ወደ ማዳን ተልዕኮው ያመለክታል፡፡

ከዚያም፣ በሉቃስ 24፥36-49 ውስጥ፣ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ በመገለጥ ስለተከናወኑት ነገሮች እንዲመሰክሩ አበረታትቷቸዋል፡፡ መልካሙንም የንስሓ እና የይቅርታ ወንጌል ለአህዛብ ሁሉ በመስበክ ተልዕኮውን እንዲቀጥሉ ነግሯቸዋል፡፡ ከዚያም ሉቃስ ደቀመዛሙርቱ ይህንን ሃላፊነት በአግባ እንዲወጡ የሚያስችላቸውን መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክላቸው ኢየሱስ የሰጠውን ተስፋ በመዘገብ፣ የሁለተኛውን መድብሉን፣ የሐዋርያት ሥራን መጽሐፍ መሸጋገሪያ በአግባቡ ያዋቅራል፡፡

ሉቃስ ወንጌሉን የሚደመድመው በ24፥50-53 ውስጥ፣ ኢየሱስ በአካል ወደ ሰማይ ማረጉን በመናገር ነው፡፡ በዚህም ተዓምር ምክንያት ደቀመዛሙርቱ እግዚአብሔርን አመሰገኑ፣ አመለኩ ደስም አላቸው፡፡ በሉቃስ 2፥10 መልአኩ አውጆት የነበረው የመልካሙ የምሥራች ደስታ

በመጨረሻው ለእግዚአብሔር ልጆች እውን ሆነ፡፡ ከሞት የተነሣው፣ ድል አድራጊው ጌታ ኢየሱስ አዳኛቸው ሆነ፡፡

ስለዚህ አህዛብ አማኞች ኢየሱስን ለመከተል በመወሰናቸው ትክክለኛ ምርጫ ያደረጉ መሆኑን ሊያረጋግጥላቸው ሉቃስ ጻፈ፡፡ በወንጌሉ ውቅርና ይዘት አማካይነት፣ የኢየሱስ ሕይወት እያንዳንዷ ገፅታ እግዚአብሔር መንግሥቱን የመመሥረቱ አካል መሆኑን ሉቃስ አሳይቷል፡፡ እርሱ ኢሳያስ የተነበየውን ሊፈፅም የመጣ እግዚአብሔር ልጅ ደግሞም የዳዊት ልጅ ነው፡፡ ኢየሱስ አህዛብን ሁሉ በእርሱ አገዛዝ ስር ለማድረግ ማንም ሊያቆመው የማይችል የጸጋና የምህረት ጉልበት አለው፡፡ እርሱ በእውነት የእግዚአብሔርን መንግሥት አምጥቷል፡፡ ለሰውም ዘር በሙሉ ድነትን አስገኝቷል፡፡ በእርሱ የሚታመኑትንም ሁሉ በእውነት ሊያድን ችሏል ያድናልም፡፡

የሉቃስን ወንጌል ዳራ፣ ውቅር እና ይዘት ከምመርን፣ አሁን የመጨረሻውን ርዕሳችንን ለመመልከት ተዘጋጅተናል፡፡ በትምህርታችን በዚህኛው ክፍል ውስጥ፣ ሉቃስ አፅንዖት የሠጠባቸውን ዐበይት መሪ ሃሳቦች እንመረምራለን፡፡

# ዐቢይ መሪ ሃሳቦች

በጥቅሉ፣ ሦስቱም ተመሳሳይ ወንጌላት ማለትም፣ ማቴዎስ፣ ማርቆስ እና ሉቃስ የጋራ ማእከላዊ መሪ ሃሳብ አላቸው፡፡ ያም፣ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚያመጣ ነው፡፡ ሆኖም እያንዳንዳቸው ይህንን ማእከላዊ ሃሳብ በተለያየ መንገድ ይገልፁታል፡፡ ስለዚህም ይህንን ሀሳብ በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ስንመረምር፣ ሉቃስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ከድነት ጋር አያይዞ በሰጠው መግለጫ ላይ እናተኩራለን፡፡

ሉቃስ መዳን፣ ማዳን፣ ድነት፣ እና አዳኝ የሚሉትን ቃላት ከሌሎቹ ወንጌላት በበለጠ ቢያንስ 25 ጊዜ ተጠቅሞባቸዋል፡፡ ያለ ክርስቶስ ባለንበት አሳዛኝ ሁኔታና፣ ነፃ አውጪ የሚያስፈልገን በመሆኑ ላይ አፅንዖት አድርጓል፡፡ እናም የእግዚአብሔር መንግሥት የእኛ ታላቅ መዳን እንደሆነ አስተምሯል፡፡

ድነት የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን በተነገረው መሲሃዊ ተስፋ ውስጥ ስር የሰደደ ሃሳብ ነው፡፡ ከከፉ ጭቆና እና  በኃጢአት ምክንያት ከሚጠብቀን ፍርድ ነፃ መውጣት ብለን ልንፈታው እንችላለን፡፡ በብሉይ ኪዳን፣ በተለይም በነቢያት ውስጥ፣ በኃጢአት ምክንያት ከሚመጣባቸው ጣጣና ከራሱም ከኃጢአት መሲሁ በስተመጨረሻው እንደሚያድናቸው እግዚአብሔር ህዝቡን አስተምሯል፡፡

ሉቃስ በድነት ላይ ከሰጠው አጽንዖት ጋር በሚጣጣም መንገድ፣ የሉቃስን ወንጌል ዐቢይ መሪ ሃሳቦች ከክርስቶስ የማዳን ሥራ ጋር በሚያያዝ መንገድ በሦስት ክፍሎች ከፍለን እንመለከተዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ስለ ግለ ድነት ሉቃስ የሰጠውን ማብራሪያ እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ እግዚአብሔርን እንደ አዳኝ የገለጸበትን እናያለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ የዳኑትን ሰዎች ዓይነት እንቃኛለን፡፡ ሉቃስ ስለ ድነት በሰጠው መግለጫ እንጀምር፡፡

# የድነት መግለጫ

በጠቅላላው ወንጌሉ፣ ግለ ድነት በተቀዳሚነት የሰዎችን ሁኔታ ፍፁም የመቀየር ጉዳይ እንደሆነ ሉቃስ አሳይቷል፡፡ ስብዕናቸውንና በእግዚአብሔር ዘንድ ያላቸውን አቋም ደግሞም ዕጣ ፈንታቸውን መቀየርና ከመረገም ይልቅ የተባረኩ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡

ሁላችን ኃጢአተኞች ሆነን ተወልደናል፡፡ በውጤቱም፣ በእግዚአብሔር የተረገምንና ለዘላለምም ጥፋት የተመደብን ሆነናል፡፡ ወንጌል ግን የኃጢአትን ይቅርታ ያስገኝልናል፣ ስለዚህም እግዚአብሔር ዳግመኛ ሊረግመን የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ ሉቃስ በተደጋጋሚ እንደሚያስቀምጠው፣ ድነት በእኛና በእግዚአብሔር ዘንድ ዕርቅ ነው፡፡ እናም ባገኘነው አዲስ ሞገስ፣ ኢየሱስ ተመልሶ ሲመጣ የምንወርሰውን በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ዘላለማዊ በረከትን እንቀበላለን፡፡ በዚያች አዲስ ምድር፣ ህመም ወይም ሞት ወይም እጦት ወይም ስቃይ ጨርሶ አይኖርም፡፡ ሕይወታችን አሁን ምንም መልክ ይኑረው፣ በሚመጣው ዓለም ግን ባለጠጎችና የታደሉ እንሆናለን፡፡

> **የሉቃስ ወንጌል አንባቢዎች በኢየሱስ ሕይወትና አገልግሎት ማህበራዊ አውድ ውስጥ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ተፅዕኖ የመፍጠር አቅም ላልነበራቸው ሰዎች ማለትም፣ ሴቶች፣ አህዛብ እና ልጆች ኢየሱስ ለየት ያለ አትኩሮት ያደርግ እንደነበር ደጋግመው ይገልፃሉ፡፡ እኔ እንደማስበውም፣ ለዚህ ነገር ጽኑ የሆነ ነገረ-መለኮታዊ ምክንያት ይኖራል፣ ያም ሉቃስ የእግዚአብሔርን መንግሥት የመጨረሻው ዘመን አገዛዝ ደካሞችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ከመሆኑ እውነታ አንፃር ተረድቶታል የሚለው ነው፡፡ እናም፣ በውጤቱ፣ ኃያላንን ስፍራ የሚያሳጣ፣ እንዲያውም ነገሩን የተገላቢጦሽ የሚያደርግ ነው፡፡ ለነገሩ፣ ይህ እውነታ፣ የተገላቢጦሹ ነገር የወንጌላት፣ ወይም የአዲስ ኪዳን ወይም የመጨረሻው ዘመን ወይም የነገረ-ፍፃሜ ልዩ ጉዳ ብቻም አይደለም፡፡ ታውቀላችሁ፣ "የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናት" የሚለው እውን ነው፡፡ ይህንን ሃሳብ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መገለጦች ሁሉ ውስጥ ታገኙታላችሁ፡፡ ለምሳሌ የዘፍጥረት መጽሐፍ፣ ደጋግሞ እንደሚሳየን፣ ሁለተኞቹ ልጆች ከበኩሮቹ ይልቅ ይመረጡ ነበር፡፡ ይህ እንግዲህ ይጠበቅ የነበረው የተገላቢጦሽ ነው ማለት ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ከተመዘገቡት ሁሉ ይጠበቅ የነበረው የተገላቢጦሽ የመሆኑን ነገር የጠቀስነው ለምሳሌ ያህል ብቻ ሲሆን፣ እንደማስበውም ሉቃስ ሊያሳይ የፈለገው የእነዚያ ሁሉ ፍፃሜ ወደ ከፍተኛው እርከን ወይም ሙላት የደረሰ መሆኑን፣ በአዲስ ኪዳንም የምናገኘው የዚህ የተገላቢጦሽ ነገር ማለትም ኃያላን ቀርተው ደካሞች ሞገስ የማግኘታቸው ነገር በትልቁ ደምቆ የተከበረ መሆኑን ነው፡፡ (ዶ/ር ዴቪድ ባወር)**

ይህንንም በሉቃስ 7 ውስጥ ተመልሳችሁ ማየት ትችላላችሁ፣ እርሱ በእውነት መሲሁ መሆኑን እንዲጠይቁለት ዮሐንስ መልእክተኞች ልኮ ነበር፡፡ ኢየሱስም የመለሰለት ከኢሳያስ 61፥1-2 በመጥቀስ ነበር፡፡ ተመሳሳዩን ምንባብ የአደባባይ አገልግሎቱን ሲጀምር በምኩራብ ውስጥ አንብቦታል፡፡ በሉቃስ 7፥22 ኢየሱስ የሰጠውን ምላሽ አንብቡ፡፡

***...ዕውሮች ያያሉ፥ አንካሶችም ይሄዳሉ፥ ለምጻሞችም ይነጻሉ፥ ደንቆሮዎችም ይሰማሉ፥ ሙታንም ይነሣሉ፥ ለድሆችም ወንጌል ይሰበካል፤ ... (ሉቃስ 7፥22)***

በዚህ ስፍራ ኢየሱስ የጠቀሰው ነገር ሁሉ የድነት ገጽታ ሲሆን፣ ከከፋ ሁኔታ ወደ መልካም ሁኔታ መዛወር ነው::

በአዲሲቷ ምድር፣ እነዚህ ክፉ ሁኔታዎች ጨርሶ ይወገዳሉ:: አሁንም እንኳን፣ ድነት የእነዚህን ዘላለማዊ በረከቶች ቅምሻ ያቋድሰናል:: በድነት ያገኘነው ለውጥ ግን በውጫዊ ሁኔታዎቻችን የሚወሰን አይደለም:: ውስጣችንንም ይለውጣል:: በሉቃስ 6፥27-36 ኢየሱስ እንዳለው:-

***.....ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ ለሚጠሉአችሁ መልካም አድርጉ፥***

***የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ስለሚበድሉአችሁም ጸልዩ። ....***

***ነገር ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ መልካም አድርጉ፤ ምንም ተስፋ ሳታደርጉም አበድሩ፥ ዋጋችሁም ታላቅ ይሆናል፥ የልዑልም ልጆች ትሆናላችሁ፥ እርሱ ለማያመሰግኑ ለክፉዎችም ቸር ነውና።***

***አባታችሁ ርኅሩኅ እንደ ሆነ ርኅሩኆች ሁኑ። (ሉቃስ 6፥27-36)***

የመንግሥቱ በረከቶች የሚለውጡት ውጫዊ ነገሮችን ብቻ አይደለም:: በተጨማሪም የዳኑትን ሰዎች ባህርይና አመለካከት ሁሉ ይቀለብሳሉ:: ውጫዊ ለውጦቹ እንደሚገለጡ ሁሉ ውስጣዊ ለውጦቹም በአሁኑ ዓለም በከፊል ይገለጣሉ፣ በሚመጣው ዓለም ደግሞ በሙላት ይገለጣሉ:: አሁን ግን፣ በተለየ መንገድ ማሰብና ማድረግን ልንጀምር ይገባናል፣ ምክንያቱም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተናልና፣ ዓለምንም የምንመለከተው በአዲስ ዐይን ነው:: እነዚህ ለውጦች በኃጢአት ምክንያት ከመጣብን ጣጣነ ከወቅቱ እርኩሰት ፈፅሞ ነጻ በምንወጣበት በመንግሥተ-ሰማያትም ይቀጥላሉ:: ኢየሱስ ዳግመኛ ተመልሶ በአዲሲቷ ምድር አዲስ አካልን ሲያለብሰን ወደ ሙላት ይመጣሉ::

እነዚህ የድነት በረከቶች በሉቃስ ወንጌል ደጋግመው ለምን ማብራሪያ ተሰጠባቸው ብንል ለድነት ተገቢ የሆነው ምላሽ ደስታ በመሆኑ ነው:: ይህንን የምናይበት አንዱ መንገድ ሉቃስ በዘገባቸው በርካታ መዝሙሮች በኩል ሲሆን፣ ለምሳሌ በሉቃስ 1፥68-79 የዘካርያስ መዝሙር፣ በሉቃስ 1፥46-55 የማርያም መዝሙር እና በሉቃስ 2፥29-32 የስምዖን መዝሙር ይጠቀሳሉ:: በድነት ደስ መሰኘት በተጨማሪም በመላእክቱ አዋጅም ውስጥ፣ ለምሳሌ በሉቃስ 1፥14 ለዘካርያስ በተነገረው መልእክት ውስጥ፣ በሉቃስ 2፥10-11 ለእረኞች በታወጀው የመልካሙ ዜና ብስራት ተገልጧል:: ኢየሱስ ስለ ጠፋው በግ፣ ስለ ጠፋው ሳንቲም እና ስለ ጠፋው ልጅ ምሳሌ ባቀረበበት ምዕራፍ 15 ውስጥ ደስታ ቋሚ መሪ ሃሳብ ነው:: ኢየሱስ የደስታን ምላሽ በሉቃስ 6፥21-23 ያጠቃለለው በዚህ መንገድ ነው:-

*… እናንተ አሁን የምታለቅሱ ብፁዓን ናችሁ፥ ትስቃላችሁና። …በዚያን ቀን ደስ ይበላችሁ ዝለሉም… (ሉቃስ 6፥21-23)*

እግዚአብሔር ድነትን ለእኛ የደስታ ምክንያት እንዲሆን ወስኖታል፡፡ ኃጢአታችን ታጥቧልና፣ ከእርሱ ጋር ሰላም የሞላበት ግንኙነት አለንና የመንግሥቱንም በረከቶች ተቀብለናልና ደስ እንዲለን ይፈልጋል፡፡ ይህ መሪ ሃሳብ ለሉቃስ ወሳኝ በመሆኑ ወንጌሉንም የደመደመው በዚያው ነው፡፡ በሉቃስ 24፥52-53 ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲያርግ ደቀመዛሙርቱ ምን እንዳደረጉ የዘገበውን አድምጡ፡-

*እነርሱም፤ … በብዙ ደስታ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፥*
*ዘወትርም እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እየባረኩ በመቅደስ ኖሩ።*
*(ሉቃስ 24፥52-53)*

**እግዚአብሔርን እንደማንነቱ ስናየው፣ ጌታ መልካም መሆኑን ስንቀምስና ስናይ፣ ወደ ደስታ ሊመራን፣ ወደ ሃሴትም ሊመራን ይገባል፡፡ ለሚስቴ አበባ ባመጣላት እና “የኔ ማር፣ ጥቂት አበቦች እኘሁልሽ፣ ምክንያቱም እነዚህን ለአንቺ መስጠት ይገባኛል” ብላት፣ ይህ ዐይነቱ ነገር እርሷ የምትፈልገው ዐይነት አይደለም፡፡ ይልቁኑ በትልቅ ደስታና ሃሴት ለእርሷ ካለኝ ከበሬታ በመነጨ መንገድ ሊቀርብ ይገባዋል፡፡ እናም፣ በእግዚአብሔር ያለን መደሰት የእርሱን ማንነት በእርግጥ የማወቃችን መግለጫ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በእግዚአብሔር መደሰት፣ ማለት በክርስትና ሕይወታችን ወሳኝ ነገሮች ውስጥ ነእርሱ እርከት መሰኘት ነው ማለት ነው፡፡ (ዶ/ር ኬ. ኤሪክ ቶኔስ)**

ይህንን የድነት መግለጫ በልቡናችን ይዘን፣ ወደ ሁለተኛው ዐቢይ መሪ ሃሳባችን ማለትም እግዚአብሔር እንደ አዳኝ ሉቃስ ወደ ሰጠው አፅንዖት እንሸጋገር፡፡

# እግዚአብሔር አዳኝ

እግዚአብሔርን እንደ አዳኝ በሦስት ደረጃዎች እንመለከታለን፡፡ ድነት የሚመጣው በእግዚአብሔር ኃይል፣ እንደ እግዚአብሔር ዕቅድ እና በእግዚአብሔር ልጅ በኩል መሆኑን እናያለን፡፡ በመጀመሪያ ድነት የሚመጣው በእግዚአብሔር ኃይል መሆኑን እንመልከት፡፡

## የእግዚአብሔር ኃይል

የሉቃስ ወንጌል ደጋግሞ የሚያስተጋባው እግዚአብሔር የህዝቡ አዳኝ ነው የሚለውን የብሉይ ኪዳን ሃሳብ ነው፡፡  ለምሳሌ፣ ይህ ሃሳብ የሉቃስ ወንጌል የመክፈቻ ምዕራፎች ገዢ ርዕስ ሲሆን፣ የመጽሐፉን አጠቃላይ ድምፅ የሚቃኝ ነው፡፡ በሉቃስ 1፥47 ማርያም ሃሴት ያደረገችው እግዚአብሔር አዳኟ በመሆኑ ነው፡፡ በሉቃስ 1፥68-79 እግዚአብሔር ስለሚያመጣው ድነት ዘካርያስ ዘምሯል፡፡ በሉቃስ 2፥29-30 ስምዖን ሕፃኑን ኢየሱስ ታቅፎ ምን እንደተናገረ አድምጡ፡

*ጌታ ሆይ፥ አሁን እንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ፤*
*ዓይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና፤*
*(ሉቃስ 2፥29-30)*

ስምዖን እግዚአብሔርን ሉዓላዊ ጌታ ወይም በግሪኩ ዴስፖታ (despota) በማለት የጠቀሰው ሲሆን፣ ይህም እግዚአብሔር በፍጥረቱ ሁሉ ላይ ያለውን ኃይልና ሥልጣን ያሳስባል፡፡ "ማዳንህን" በሚለው አባባልም፣ እግዚአብሔር ኃይሉን የሚጠቀመው ለማዳን መሆኑን ስምኦን ያመለክታል፡፡

ይኸው ተመሳሳይ መሪ ሃሳብ በተቀሩትም የሉቃስ ወንጌል ክፍሎች ይዘልቃል፡፡ ለምሳሌ፣ በሉቃስ 3፥6 ውስጥ፣ መጥምቁ ዮሐንስ የእግዚአብሔርን ማዳን ምድርን ሁሉ በኃይሉ በሚያድስበት አውድ ውስጥ ያውጃል፡፡ በሉቃስ 18፥26-27 ውስጥ፣ ድነት በሰው ፈቃድ እንደማይመጣ እና ለእግዚአብሔር ግን ሁሉ እንደሚቻል ኢየሱስ አስተምሯል፡፡

እግዚአብሔር ሁሉን እንደሚገዛ አንባቢዎቹ እንዲያውቁ ሉቃስ ይፈልጋል፡፡ እናም ስለዚህ፣ ድነት በሰው ብርታት፣ ዕውቀት፣ ቁርጠኝነት ወይም ሀብት አይገኝም፡፡ በእርሱ ኃይል የሚፈፀም የእርሱ ሥራ ነው፡፡ ሰዎች ከእርሱ ፍርድ ነፃ እንዲሆኑ ማድረግ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ሰዎችን ከውስጥ መለወጥ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ መንግሥቱን ወደ ምድር ለማምጣት የሚያስፈልገው ኃይል ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ በዚያ መንግሥት በረከትም ህዝቡን መባረክ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡

ድነት የሚገኘው በእግዚአብሔር ኃይል ብቻ እንደሆነ አፅንዖት ከመስጠት ባሻገር፣ ድነት የእግዚአብሔር ዕቅድ አካል እንደሆነ ሉቃስ አስተምሯል፡፡

## የእግዚአብሔር ዕቅድ

ለምሳሌ፣ በሉቃስ ምዕራፍ 4 ውስጥ ኢየሱስ የአደባባይ አገልግሎቱን ሲጀምር፣ ከኢሳያስ 61፥1-2 አንብቧል፡፡ ያም ትንቢት በዚያን ወቅትና ስፍራ በእርሱ እንደተፈፀመ በመናገር ህዝቡን አስደነቀ፡፡ ሉቃስም በተቀሩት የወንጌሉ ክፍሎች፣ የኢየሱስ ድራማዊ የሕይወት ሁነቶች በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ ፍፃሜ መሆኑን በማሳየት ድነት የእግዚአብሔር ዕቅድ አካል መሆኑን ገልጧል፡፡ በሉቃስ 24፥44 ውስጥ በአደባባይ አገልግሎቱ ማብቂያ አካባቢ ኢየሱስ የተናገረውን አድምጡ፡

*… በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል… (ሉቃስ 24፥44)*

ብሉይ ኪዳን በጠቅላላው የሚናገረው እግዚአብሔር በልጁ በኩል ስለሚፈፅመው ማዳን ነው፡፡ ሰዎችን በዚህ መንገድ ማዳን የእግዚአብሔር ዕቅድ ሆኖ ለዘወትር ይዘልቃል፡፡

ድነት የእግዚአብሔር ዕቅድ ፍፃሜ መሆኑን ሉቃስ ያሳየበት ሌላው መንገድ ኢየሱስ ያደረጋቸው ነገሮች ሁሉ እጅግ አስፈላጊ መሆናቸውን ደጋግሞ በማመልከት እግዚአብሔር የሚፈልጋቸው እንዲያውም እንዲከናወኑ የወሰነባቸው መሆኑን መግለጥ ነው፡፡ አንድ ምሳሌ ብንወስድ፣ በሉቃስ 9፥22 ውስጥ፣ ኢየሱስ መከራውንና ሞቱን የገለጠበትን መንገድ አድምጡ፡

> ***የሰው ልጅ ብዙ መከራ ሊቀበል በሽማግሌዎችም በካህናት አለቆችም በጸፎችም ሊጣል ሊገደልም በሦስተኛውም ቀን ሊነሣ ይገባዋል (ሉቃስ 9፥22)***

ሊሆን ስላለው ነገር ኢየሱስ ሲያብራራ፣ "ይገባዋል" የሚለውን ቃል ተጠቅሟል፣ ይህም ዴዩ (dei) የሚለው የግሪክ ቃል አቻ ሲሆን ፍቺውም "አስፈላጊ ነው" የሚል ነው፡፡ ለምን አስፈላጊ ሆነ? ብንል፣ እግዚአብሔር ስለሚፈልገው ነው፡፡ በኢየሱስ ላይ የሆነው ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ህዝቡን ለማዳን ያወጣው የቀደመው ዕቅዱ አካል ነው፡፡

እግዚአብሔር አዳኛችን መሆኑን የምንገልጥበት ሦስተኛው ነጥብ ድነት የሚመጣው በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት መሆኑ ነው፡፡

## የእግዚአብሔር ልጅ

የሉቃስ ወንጌል ደጋግሞ የሚያረጋግጥልን ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ የኢየሱስ ልጅነት ሰው የሆነው አምላክ ተብሎም ይጠቀሳል፣ ይህም በሉቃስ 1፥32-35 መወለዱ በመላእክት እንደታወጀው መሆኑ ነው፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ፣ በሥልጣኑ ላይ አፅንዖት ይሰጣል፡፡ ይህንንም በሉቃስ 3፥22 ውስጥ፣ በጥምቀቱ ወቅት እግዚአብሔር ከሰማይ ማረጋገጫውን ሲሰጥ እና በሉቃስ 9፥35 ውስጥ በመለወጥ ተራራ ላይ ሰዎች ልጁን እንዲሰሙ ባዘዘበት ወቅት እንመለከተዋለን፡፡ በሌላ ጊዜም ደግሞ እንደ መሲሃዊ የእግዚአብሔር ንጉሥ በመጨረሻዋ ራት ወቅት በሉቃስ 22፥29 ውስጥ ጠቅሶታል፡፡

ኢየሱስ እንደ እግዚአብሔር ልጅ የተጣቀሰባቸው እነዚህ ማጣቀሻዎች ሁሉም ቢያንስ አንድ የጋራ ነገር አላቸው፡ ሁሉም የሚያመለክቱት ኢየሱስ፣ እግዚአብሔር ድነትን በእርሱ አማካይነት የሚያመጣበት መሆኑን ነው፡፡ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወደ ምድር በማምጣት በሞቱ ህዝቡን ከኩነኔ ለማዳን ወደ ዓለም የተላከው የእግዚአብሔር ልጅ ነው፡፡

አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖች አብ እኛን የሚጠላን እናም ኢየሱስ ደግሞ በእኛ ምትክ ለመቆም በአባቱ ላይ ያመፀ ልጅ አድርገው በተሳሳተ መንገድ ያስባሉ፡፡ ኢየሱስ ሊያድን የመጣው ግን አብ ልኮት ነው፡፡ አዎን፣ ኢየሱስ በእውነት አዳኛችን ነው፡፡ በእውነትም ከአብ ፍርድ አድኖናል፡፡ ሆኖም ግን እርሱ ያመጣው ማዳን ግን የመነጨው ከአብ መሆኑን መረዳት ወሳኝ ነው፡፡ እንደ እግዚአብሔር ልጅ፣ ኢየሱስ የፈፀመው አብ ያዘዘውን ብቻ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ለመፈፀም የእግዚአብሔርን ኃይል ተጠቅሟል፡፡ በዚህም መንገድ፣ የኢየሱስ የማዳኑ ሥራ ያረጋገጠልን ታላቁ አዳኛችን እግዚአብሔር አብ መሆኑን ነው፡፡

ሉቃስ ስለ ድነት እና እግዚአብሔር አዳኛችን ስለ መሆኑ የሰጠውን መግለጫ ከተመለከትን፣ ወደ ሉቃስ ወንጌል ሦስተኛ ዐቢይ ርዕስ፡ ስለ ዳኑት የተለያዩ ሰዎች ወደምንመለከትበት እንሸጋገር፡፡

# የዳኑ ህዝቦች

ኢየሱስ በዘመኑ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ከበሬታ ስፍራ ወይም ኃይል የነበራቸውን ሰዎች አድኖ ቢሆን ኖሮ ማንም አይደንቀውም ነበር፡፡ በእግዚአብሔር የህጉ ጽሕፈትም የተረጋገጠላቸውን ለምን አዳነ ብሎ የሚገረምም አይኖርም፡፡ የአይሁድ ህዝብም ጥንቱኑ ያቃለሉዋቸውን ረግሞ ቢሆን ኖሮም ወይም ድርሻቸውን ባለመወጣት ድካም የታየባቸውን በረከት ከልክሎ ቢሆን የሚደንቀው አይኖርም፡፡ ኢየሱስ ያደረገው ግን ይህን አልነበረም፡፡ ከሉቃስ ወንጌል ዐቢይ ሃሳቦች አንዱ ኢየሱስ ስለአዳናቸው እና አስገራሚ ክብር ስለ ሰጣቸው የተደነቁ ሰዎችን ትኩረት መሳብ ነበር፡፡

> ***ስለ ሉቃስ ትረካ ሊጠቀሱ ከሚገባቸው አንዱ ከሁሉ በሚያንሱት፣ የመጨረሻ በሆኑት እና በጠፉት ላይ ማትኮሩ ሲሆን፣ እንዲያውም ከዐቢይ ሃሳቦቹ አንዱ የመለወጥ መሪ ሃሳብ ነው፡፡ ከሁሉ የሚያንሱት፣ የመጨረሻ የሆኑት እና የጠፉት የመጀመሪያ፣ ተቀዳሚ እና በእግዚአብሔር መንግሥት ስፍራ ያላቸው ሊሆኑ ነው፡፡ ሉቃስ በወንጌል ሥነ-ምግባራዊ ገፅታ ላይ ማትኮር ፈቅዷል፡፡ የኢየሱስ አገልግሎት መለያ በሆኑት ላይ ማለትም የሚመሰገን ወይም የደግነት ሥራ በሆኑት ላይ አትኩሯል፡፡ የሁለት መድብል ሥራዎቹ በሆኑት የሉቃስና የሐዋርያት ሥራ መጻሕፍት የምንመለከተው ለድሆች፣ ለሴቶች፣ ለታመሙትና እና ለአረጋውያን ግድ መሰኘቱን ነው፡፡ እነዚህን ከመሳሰሉ ነገሮች አንፃር የሉቃስ/የሐዋርያት ሥራ መጻሕፍት ከሌሎቹ ወንጌላት ይልቅ ጠንከር ያለ አፅንኦት የሰጡ መሆናቸው አያጠያይቅም፡፡ ማለቴ፣ ከማቴዎስ ይልቅ የኢየሱስን ደስታ ስንመለከት፣ ማቴዎስ “በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁአን ናቸው” በማለት ሲያስቀምጠው ሉቃስ ግን “ድሆች ብፁአን ናቸው” በማለት ያስቀምጠዋል፡፡ ሉቃስን በእውነት ግድ የሚለውም ይህ ነበር፡፡ ስለዚህ ግድ የተሰኘበት ምክንያትም በኢየሱስ አማካይነት የተገኘው መቤዠት ብቻ ሳይሆን ፍትህም እንደሆነ ያምን ስለነበረ ነው፡፡ በሰው ዘር ውድቀት ምክንያት የመጣውን የማኅበረሰቡን ቀውስ የማስተካከሉ ሥራ በኢየሱስ እየተከናወነ መሆኑን በማሳየት ኢየሱስ የዓለም አዳኝ መሆኑን አፅንዖት ሊሰጥበት ወድዷል፡፡ እንዲያውም፣ እርሱ የእያንዳንዱ ሰው አዳኝ ነው፡፡ ይህም በእኛ ዘመን ሁሉንም በአንድ ጊዜ መሸመት የምንለው ዓይነት እናንተ በማኅበረሰቡ ውስጥ የሰው ሁሉ ቁንጮ ወይም በጣም የተማሩ ሰዎች አሊያም ደግሞ እጅግ ታዋቂ ብትሆኑም ወይም በተቃራኒው የመጨረሻዎቹ መጨረሻ ብትሆኑም፣ ኢየሱስ ለሁሉ ነው እናም ሉቃስ አፅንዖት መስጠት የፈለገው በዚያ ላይ ነው፡፡*** (ዶ/ር ቤን ዊተሪንግተን)

በዚህ ትምህርት ለያዝነው ዓላማ፣ ሉቃስ ደግሞ ደጋግሞ ትኩረታቸውን በሳበው አራት ዓይነት በአድናቆት የተሞሉ ሰዎችን በመመልከቱ ላይ ብቻ እንገደባለን፣ የምንጀምረውም ከአህዛብ ነው፡፡

አህዛብ በስተመጨረሻው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንደሚመጡና ድነትንና በረከትንም እንደሚቀበሉ ብሉይ ኪዳን ይናገራል፡፡ በእስራኤል ዘመን የነበሩ አይሁድ ግን አህዛብን ዝቅ አድርገው ይመለከቱና ከእግዚአብሔር መንግሥት በረከቶች የተወገዱ አድርገው ይቆጥሩ ነበር፡፡

ሉቃስ ወንጌሉን በጻፈበት ወቅት፣ በመላው ዓለም የምትገኘው ቤተክርስቲያን ከአህዛብ የተለወጡ አማኞችን በብዛት የያዘች ነበረች፡፡ በታሪክ ዘመናትም፣ እግዚአብሔር አህዛብን ለመባረክ ያለውን ዓላማ በሚያስገርም መንገድ አሳይቷል፡፡ በዚህ ትምህርት አስቀድመን እንደተመለከትነው፣ ሉቃስ የጻፈበት አንዱ ምክንያት አህዛቦች ክርስቲያን በመሆናቸው ስህተት እንዳልፈፀሙ ሊያረጋግጥላቸው በመፈለጉ ነው፡፡ ስለዚህም፣ በወንጌሉ በጠቅላላ፣ አትኩሮት ያደረገው ድነት ወደ አህዛብ በተስፋፋባቸው እና ከብሉይ ኪዳን ተስፋዎች ጋር የሚስማሙ ነገሮች በተፈፀሙባቸው ነገሮች ዙሪያ ነው፡፡

ለምሳሌ፣ በሉቃስ 2፥10-14 ውስጥ፣ የወንጌሉ ደስታ "ለህዝቦች ሁሉ" እና "በምድር ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉ"መሆኑን መላእክት አውጀዋል፡፡ የእስራኤል አዲሱ ንጉሥ የሚወለደው አይሁድን ለማዳን ነው ከማለት ይልቅ፣ መላእክቱ የተናገሩት በዓለም አቀፋዊ ዘይቤ ነው፡፡ በሉቃስ 2፥32 ውስጥ፣ ህፃኑ ኢየሱስ "ለአሕዛብ ሁሉን የሚገልጥ ብርሃን" መሆኑን ስምዖን አውጇል፡፡ አራቱም ወንጌላት በመጥምቁ ዮሐንስ ታሪክ ውስጥ ኢሳያስ 40 ሲጠቅሱ፣ ሉቃስ 3፥6 ብቻ "የሰው ዘር በሙሉ የእግዚአብሔርን ማዳን ያያል" የሚሉትን ቃላት አካትቶ ይጠቅሳል፡፡

ሉቃስ በተጨማሪም አይሁድ እንደ ጠላት የሚቆጥሯቸው፣ ሳምራውያንም፣ እንደሚድኑ ይጠቅሳል፡፡ ለምሳሌ፣ በሉቃስ 17፥11-19 ውስጥ፣ ኢየሱስ ዐሥሩን ለምፃም ፈውሷል፣ ወደ እርሱ ተመልሶ ያመሰገነው ሳምራዊው ለምፃም ብቻ ነው፡፡ በሉቃስ 10፥30-37 የሚገኘውን የደጉን ሳምራዊ ታሪክ የዘገበው ሉቃስ ብቻ ሲሆን፣ ሳምራዊው ብልንጀራን የመውደድ ተምሳሊት ሆኗል፡፡

ከዚህም ባሻገር፣ አህዛብ ኢየሱስን እንደ አዳኝ ስለሚቀበሉበት ወቅት ሉቃስ ዘግቧል፡፡ ለምሳሌ በሉቃስ 7፥9 ውስጥ፣ ኢየሱስ ስለ ሮማዊው መቶ አለቃ እንዲህ ብሏል፡

***በእስራኤልስ እንኳ እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት አላገኘሁም (ሮሜ 7፥9)***

በዚህ ትምህርት ቀደም ብለን እንዳየነው፣ ሉቃስ የኢየሱስን የትውልድ ሃረግ ወደ ኋላ ወስዶ፣ ኢየሱስ የአዳምን ዘር በሙሉ፣ ኤሁድና አህዛብን ሁሉለማዳን እንደመጣ ለማመልከት ከአዳም ጋር አያይዞታል፡፡

በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ድነትን ያገኙ ሁለተኛዎቹ አስገራሚ ሰዎች ኃጢአተኞች ናቸው፡፡ የሰው ዘር በጠቅላላ ኃጢአተኛ ነው፡፡ ሆኖም በኢየሱስ ዘመን የአንዳንዶቹ ኃጢአት ግን ትልቅና አደባባይ የወጣ በመሆኑ እነዚህም ሰዎች በአይሁድ ማኅበረሰብ ይገለላሉ፣ ለምሳሌ እንደ አመንዝራዋ ሴት በሉቃስ 736-50፣ ቀረጥ ሰብሳቢው ዘኬዎስ በሉቃስ 19፥1-9 ይጠቀሳሉ፡፡ ቀረጥ ሰብሳቢዎች ኃጢአተኞች ነበሩ ምክንያቱም ኑሮአቸውን ለማሸነፍ ሲሉ ከአገራቸው ሰዎች መንግሥት ያልጣለባቸውን ከመጠን ያለፈ ቀረጥ ይሰበስቡ ስለነበር ነው፡፡ ኢየሱስ ግን እነርሱንም ለማዳን መጣ፡፡ በእምነት ንስሐ ለሚገባ ሁሉ ድነትን ለመስጠት በእጅጉ ይሻ ነበር፡፡

ለምሳሌ፣ በሉቃስ 5፥29-32 የተጠቀሰውን ይህን ታሪክ አድምጡ፡

> *ሌዊም በቤቱ ታላቅ ግብዣ አደረገለት፤ ከእነርሱም ጋር በማዕድ ተቀምጠው የነበሩ ከቀራጮችና ከሌሎች ሰዎች ብዙ ሕዝብ ነበሩ።*
> *ፈሪሳውያንና ጻፎቻቸውም በደቀ መዛሙርቱ ላይ። ስለ ምን ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር ትበላላችሁ ትጠጡማላችሁ? ብለው አንጐራጐሩ።*
> *ኢየሱስም መልሶ፦ ሕመምተኞች እንጂ ባለ ጤናዎች ባለ መድኃኒት አያስፈልጋቸውም፤*
> *ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም አላቸው።*
> *(ሉቃስ 5፥29-32)*

በሉቃስ ወንጌል ድነታቸው የተመዘገበው ሦስተኛዎቹ አስደናቂ ሰዎች ሴቶች ናቸው፡፡ ኢየሱስ በኖረበት፣ ጥንታዊ የምሥራቃዊ ሜድትራኒያን ዓለም ውስጥ፣ ሴቶች በማኅበረሰቡ ውስጥ ብዙ መብት አልነበራቸውም ደግሞም ያን ያህል ዋጋም አይሰጣቸውም ነበር፡፡ ሉቃስ ግን ለእነርሱም ድነትን ኢየሱስ ወዳመጣበት መንገድ ትኩረት ያደርጋል፡፡ በሉቃስ 8፥41-53 ውስጥ፣ ኢየሱስ የኢያኢሮስን ሴት ልጅ እና ለዐሥራ-ሁለት ዓመታት ደም ሲፈሳት የነበረችውን ሴት ፈውሷል፡፡ በተጨማሪም፣ በጥንታዊው የአባቶች ዘመን የሚረዳቸው ለሌላቸውና በገሃድም ተስፋ ለሌላቸው መበለቶች ልዩ ርኅራኄን አሳይቷል፡፡ ሉቃስ 7፥11-17 እና 18፥1-8 ለእነዚህ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ኢየሱስ የነበረውን ርኅራሄና ግድ መሰኘት ይገልጥልናል፡፡

ሉቃስ የሴቶችን መዳን አጉልቶ ከገለጠባቸው ድራማዊ የማስተማር ቴክኒኮች መካከል አንዱ ትኁት የሆነችውን ሴት ከትምክህተኛው ሓይማኖታዊ መሪ ጋር በተቃርኖ ያመሳሰለበት ነው፡፡ ለምሳሌ፣ በሉቃስ 13፥14-15 ውስጥ፣ የምኲራቡን አለቃ ግብዝ ሲለው፣ በሚቀጥለው ጥቅስ ግን የጎበጠችውን ሴት “የአብርሃም ልጅ” አላት፡፡ ተመሳሳዩን ተቃርኖ በሉቃስ 7፥37-50፣ ኢየሱስ የአመንዝራዋን ሴት አምልኮ ሲቀበል ትምክህተኛውን ስምዖንን ግን ወቅሶታል፡፡

እግዚአብሔርን መውደድ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለማሳየት የገለጠበትን ላዕላይ ምሳሌ ከኢየሱስ ጓደኛ ከማርያም ጋር ሉቃስ አገናኝቶታል፡፡ በሉቃስ 10፥27 ውስጥ፣ ሁለቱ ታላላቅ ትዕዛዛት እግዚአብሔርንና ባልንጀራን መውደድ መሆኑን ኢየሱስ አስተምሯል፡፡ ከዚያም፣ ከቁጥር 38-42፣ ማርያም እግዚአብሔርን እንዴት እንደሚወደድ፣ በተለይም፣ ትምህርቶቹን በመታዘዝ በመስማት ምሳሌ አሳይታለች፡፡ ይህንን እግዚአብሔራዊ ቅድስና ያሳየው ጴጥሮስ አይደለም፣ ዮሐንስ አይደለም እናም በእርግጠኝነትየአይሁድ መሪዎችም አይደሉም ይልቁኑ ሴት ነበረች፡፡

በመጨረሻ፣ በሉቃስ ወንጌል ድነትን ያገኙ አስገራሚ የሆኑ አራተኛው የሰዎች ቡድኖች ድሆች ናቸው፡፡ ሉቃስ ወንጌሉን የሚጀምረው የማርያምና የዮሴፍ ቤተሰብ ድሃ መሆኑን በመግለፅ ነው፡፡ ይህንን ያወቅነው በሉቃስ 2፥24 መሠረት ወደ መቅደስ ይዘውት የመጡት መስዋዕት በዘሌዋውያን 12፥8 ድሆች እንዲያቀርቡ የተነገረውን መስዋዕት በመሆኑ ነው፡፡

ኢየሱስ ለድሆች ግድ የሚለው መሆኑን በሉቃስ 12፥13-34 ስለሞኙ ባለጠጋ በተናገረው ምሳሌ፣ በሉቃስ 16፥19-31 ደግሞ ስለ ባለጠጋውና ስለ አልዓዛር በዘገበው ታሪክ ውስጥ ሉቃስ አመልክቷል፡፡ ከኢሳያስ 61፥1 ጠቅሶ ኢየሱስ ያነበበበትን የሉቃስ 4፥18 ክፍል አንድ ጊዜ አድምጡ፡

*የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፤ (ሉቃስ 4፥18)*

ሉቃስ ይህንን ሁነት የዘገበ ብቸኛ የወንጌል ጸሐፊ ነው፡፡ ይህንን ያካተተውም የኢየሱስን አጠቃላይ አገልግሎት ናሙና ለማሳየት ነው፡፡ ነጥቡም የእግዚአብሔርን መንግሥት የማምጣቱ አካል ለድሆች የማዳንን ወንጌል መስበክ መሆኑን ማሳየት ነው፡፡ የፍጥረተ-ዓለሙ ፈጣሪ ማኅበረሰቡ እንኳን የገፋቸውን ለማዳን ስጋ ሆነ የሚለውን ለማመልከት ሉቃስ ልዩ ጥንቃቄ አድርጓል፡፡ አህዛብ፣ ኃጢአተኞች፣ ሴቶች እና ድሆች በአይሁድ ማኅበረሰብ ውስጥ በጣም አናሳ መብት ነበራቸው እናም የእግዚአብሔርን መንግሥት ታላላቅ በረከቶች እንዲወርሱም አይጠበቁም፡፡ ኢየሱስ ግን ይህንን የማኅበረሰብ እሴት ውድቅ አደረገው፡፡ እርሱን አዳኝና ጌታ አድርጎ የተቀበለ ሁሉ ሙሉ ተቀባይነትና ያልተገደበ በረከት እንዲያገኝ አድርጓል፡፡

**ከሁሉም የወንጌል ጸሐፍት ይልቅ ሉቃስ በእርሱ ዘመን በነበረው የፓለስታይን ማኅበረሰብ ውስጥ በተገለለሉት ቡድኖች ላይ ልዩ አፅንኦት ሰጥቷል፡፡ በተደጋጋሚም ስለ ወንዶች የተናገረውን ከሴቶች ጋር ሲያታምደው እንመለከተዋለን፡፡ ደግሞም ለሳምራውያን እና ለድሆች ልዩ አፅንኦት ሲሰጥም እንመለከተዋለን፡፡ ስለ አልዓዛርና ስለ ባለጠጋው ሰው የተዘገበው ታሪክ፣ በሉቃስ ወንጌል ብቻ የሚገኝ ሲሆን፣ ይህም ምሳሌ የሉቃስ ወንጌልን ብቸኛ ባህርይ የሚያሳይ ሆኖ እናየዋለን፡፡ የደጉ ሳምራዊ ምሳሌም በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ብቻ የምናገኘው ነው፡፡ እነዚህ የኢየሱስ ትምህርት ዘገባዎች በናዝሬት ከሰጠው የስብከት አገልግሎት ጋር በጣም ይጣጣማሉ፡፡ የሚናገረውም፣ ዛሬ ይህ መጽሐፍ በጆሮአችሁ ተፈጸመ፤ የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩትም መፈታትን፤ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ መጥቻለሁ ሲል ነው፡፡ ኢየሱስም ለደቀመዛሙርቱ የነገረው ወደ ግብዣው ሲመጡ አንካሶችንና ድሆችን እንዲጋብዙ ነው፡፡ እናም ኢየሱስ በጣም ወሳኝ ነገር ይገልጻል፣ ያም የእግዚአብሔር አምሳል ካለባቸው ከሌሎች ጋር በሚኖረን ግንኙነት፣ ጳውሎስ እንዳስቀመጠው፣ ልናስብ ከሚገባን አልፈን ከእነርሱ እንደተሻልን አድርገን ስለራሳችን ማሰብ እንደማይገባን ያመለክታል፡፡ ልናስተውል የሚገባን ኢየሱስ በጸጋ ሁሉንም የማኅበረሰብ ክፍሎች የደረሰ መሆኑን ነው፡፡ ደቀመዛሙርቱንም ያንኑ እንዲያደርጉ ጠርቷል፡፡ እኛም ያንኑ ማድረግ ይገባናል፡፡ ኢየሱስ ከአመንዝሮችና ከኃጢአተኞች ጋር በማሳለፉ ሲሳለቁበት መልስ የሰጠው፣ የመጣሁት ለጻድቃን ሳይሆን ለኃጢአተኞች ነው በማለት ነበር፡፡ ስለዚህም ጉዳዩ ኢየሱስ በእርሱ ዘመን በነበረው ማኅበረሰብ ውስጥ የእግዚአብሔርን ህዝብ የትኛውንም ማኅበረሰብ የመድረስ ተልዕኮ እንደነበረው የሚያሳይ ብቻ ሳይሆን፣ በእውን እኛ እነማን መሆናችንን እና የሚያስፈልገንም ምን እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ እኛ ሁላችን የእግዚአብሔር ጸጋ ያስፈልገናል፣ በመልካም ሥራዎቻችን ወይም በማኅበረሰቡ ውስጥ ባለን ስፍራ የእግዚአብሔርን ሞገስ ልናገኝ አንችልም፣**

**ስለዚህም ሁላችንም በእግዚአብሔር ፊት እኩል ነን እናም አንዳችን ለሌላችን በጎነትን ልናሳይና አንዳችን ወደ ሌላችን ልንደርስ ይገባናል ምክንያቱም መሻቶቻችን ተመሳሳይ ናቸውና፡፡ (ዶ/ር ግሬግ ፔሪ)**

# ማጠቃለያ

በዚህ ትምህርት፣ የሉቃስን ወንጌል ከጸሐፊውና ከቀደምት ተደራሲያኑ፣ ከተፃፈበት ወቅት፤ ከውቅሩና ከይዘቱ፤ በድነት ርእስ ዙሪያ ከሚያጠነጥኑ መሪ ሃሳቦች አንፃር መርምረናል፡፡ እነዚህን ሃሳቦች በልቡናችን ይዘን የሉቃስን ወንጌል ካነበብን፣ ስለ ፍቺው ትክክለኛ ግንዛቤ የሚኖረን ሲሆን በግል ሕይወታችን በቤተክርስቲያን እና በዓለም ለማዛመድ ይበልጥ ዝግጁዎች እንሆናለን፡፡

የሉቃስ ወንጌል ኢየሱስን አፍቃሪ የዓለም ሁሉ አዳኝ ሆኖ ወደ ምድር የመጣ የከበረው የእግዚአብሔር ልጅ አድርጎ ያቀርብልናል፡፡ ዘራቸው፣ ሃብታቸው ወይም ስፍራቸው ምንም ይሁን ምን የእግዚአብሔር የማዳን ወንጌል ለሁሉ መሆኑን ይገልፃል፡፡ የሉቃስ ወንጌል፣ በዘመኑ የነበሩት አህዛብ ክርስቲያኖች አይሁዳዊውን መሲህ በመከተላቸው ስህተት እንዳልፈፀሙ ያረጋግጥላቸዋል፡፡ በሁሉም ዘመናትም ነገሩ እውነትነት አለው፡፡ ከመጀመሪያው ምዕተ-ዓመት አንስቶ እስካሁን ድረስ፣ የቤተክርስቲያን አብዛኛው ህዝብ ከአህዛብ ወገን የሆነው አማኝ ነው፡፡ ስለዚህ እኛም አልተሳሳትንም፡፡ እናም እንደ ክርስቶስ ተከታዮች እውነተኛ መዳንን የሚያስገኝ ብቸኛ መልእክት እንዳለን በማወቅ ያንኑ ተመሳሳይ የንስሓና የእምነት የምሥራች ወንጌል በዓለም ለሚገኝ ለእያንዳንዱ ሰው የመስበክ ሃላፊነት አለብን፡፡